ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the Source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ.-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

3ኛ ዓመት፣ ቁጥር 1፣ የካቲት 2007

## በዕውቀት ላይ የተመሠረተ አስተያየት በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

‘የቤርጎ ቤቶቻችን’ ገመና... 7

ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)

በአድዋ ድል - ማንነት፣ አንድነት፣ ነጻነት... 9

ብርሃኔ አለሙ

የማሕበረሰብ አገልግሎት የልምድ ልውውጥ ጉዞ ... 8

የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ ... 6

ፈታሒ በቃሉ

# ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለዶ/ር ሙሉጌታ ክብረት የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጠ



ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሳይንስ ኮሌጅ በባዬሎጅ ት/ክፍል መምህርና ተመራማሪ ለዶ/ር ሙሉጌታ ክብረት አዘነ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ 3ተኛ የሆነውን የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጠ፡፡ ዶ/ር ሙሉጌታ ለፕሮፌሰርነት ማዕረግ የበቁት ከ30 በላይ ትርጉም ያላቸው የምርምር ውጤቶችን በተለያዩ ታዋቂ ጆርናሎች በማሳተም በመቻላቸውና የዩኒቨርሲቲው ሴኔት መመሪያ የሚጠይቃቸውን የደረጃ እድገት መስፈርቶችን በማሟላታቸው ዩኒቨርሲቲው የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል ...

የበለጠ ገጽ 2ን ይመልከቱ





BDU and ARNS Government Communication Affairs signing Memorandum of Understanding

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

ናይል
THE NILE

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የአማካሪ ቦርድ አባላት
አቶ ሞገስ አብርሃ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

ዋና አዘጋጅ:-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ም/ዋና አዘጋጆች
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

አርታኢዎች
አብነት ሰለሞን
ነብዩ ንጉሴ

ዘጋቢዎች:-
የማነ ገብሩ
ታድዮ አስማረ
ትግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

አምደኞች:-
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)
ሂሩት አድማሱ
ብርሃኔ አለሙ
አረጋዊ ሰለሞን

ግራፊክስና ሌይአውት:-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ፎቶ አንሺዎች:-
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

የኮምፒውተር ጽሁፍ:-
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቴ

ትራንስፖርት:-
ማናለ ኃይሌ
መልእክተኞች:-
ንብረት ታፈረ
ይርጋ ሻረው

ስልክ:- +251 583206088
+251 583207023

# አበይት ዜናዎች

## ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ለዶ/ር ሙሉጌታ ክብረት የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጠ

በታድየ አስማረ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በሳይንስ ኮሌጅ በባዬሎጅ ት/ክፍል መምህርና ተመራማሪ ለሆኑት ለዶ/ር ሙሉጌታ ክብረት አዘነ በዩኒቨርሲቲው ታሪክ 3ተኛ የሆነውን የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጠ፡፡ ዶ/ር ሙሉጌታ ለፕሮፌሰርነት ማዕረግ የበቁት ከ30 በላይ ትርጉም ያላቸው የምርምር ውጤቶችን በተለያዩ ታዋቂ ጆርናሎች በማሳተም በመቻላቸውና የዩኒቨርሲቲው ሴኔት መመሪያ የሚጠይቃቸውን የደረጃ እድገት መስፈርቶችን በማሟላታቸው ዩኒቨርሲቲው የፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጥቷቸዋል፡፡

ፕሮፌሰር ሙሉጌታ በባሕር ዳር ከተማ ነሐሴ 04/1956 ዓ.ም የተወለዱ ሲሆን የአንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በአፄ ሰርፀ ድንግል ት/ቤት፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጣና ሐይቅ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አጠናቀዋል፡፡ ለዩኒቨርሲቲ መግቢያ የሚሆን ከፍተኛ ውጤት በማምጣታቸው ወደ ኤርትራ አስመራ በመጓዝ በአስመራ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ድግሪያቸውን በ1978 ዓ.ም በባዮሎጂ ትምህርት አግኝተዋል፡፡

ከአስመራ ዩኒቨርሲቲ ተመርቀው ከወጡ በኂላ ወደ አርባ ምንጭ በመሄድ በቀድሞው የአርባ ምንጭ የውሃ ቴክኖሎጂ ተቋም ውስጥ በመምህርነት የተቀጠሩ ሲሆን በወቅቱ ተቋሙ የተቋቋመበት ጊዜ ስለነበር የመስራችነት ድርሻቸውም ከፍተኛ ነበር፡፡

ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ለመማር ባላቸው ፅኑ ፍላጐት በ1983 ዓ.ም የሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ካገኙ በኃላ ወደ አርባ ምንጭ ቴክኖሎጂ ተቋም በመመለስ ለሶስት ዓመታት አገልግለዋል፡፡ በ1987 ዓ.ም ወደ ቀድሞው የባሕር ዳር መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በመዛወር ለሁለት ዓመት በባዮሎጂ ት/ክፍል በማስተማር አገልግለዋል፡፡ ለትምህርት ባላቸው ፍላጎት የሶስተኛ ዲግሪያቸውን ለመስራት በ1989 ዓ.ም ወደ ኦስትሪያ ሀገር በመሄድ በ1992 ዓ.ም አጠናቀው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል፡፡

ፕሮፌሰር ሙሉጌታ በአሁን ሰአት የሁለተኛ እና የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎችን በማስተማርና በማማከር እየሰሩ ሲሆን ከመማር ማስተማር በተጨማሪ የምርምር ሥራዎችን በመስራት ከ30 በላይ የምርምር ውጤቶች በታዋቂ ጆርናሎች በማሳተም ለወጣትና አንጋፋ ተመራማሪዎች አርአያነታቸውን እያሳዩ ይገኛሉ፡፡

ፕሮፌሰር ሙሉጌታ በአርባ ምንጭ የውሃ ቴክኖሎጅ ተቋምና በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በት/ክፍል ኃላፊነት ያገለገሉ ሲሆን ከጥቅምት 1996 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1999 ዓ.ም የትምህርት ፋኩልቲ ዲን በመሆን አገልግለዋል፡፡ በተጨማሪም ከ2001 እስከ የካቲት 2002 ዓ.ም የዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክና የምርምር ምክትል ፕሬዚዳንት በመሆን በትጋት አገልግለዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲውን እንዲያገለግሉ በተጠየቁበት የሥራ፣ የምርምር፣ የካሪኩለም ቀረፃ እና ልዩ ልዩ የኮሚቴ ተግባራት ውስጥ በሰብሳቢነትና በአባልነት በመሳተፍ ለዩኒቨርሲቲውና ለሀገራቸው በርካታ ሥራዎችን አበርክተዋል፡፡ እንዲሁም በአለም ባንክ በሚደገፈው ዲአይኤፍ (DIF project) ውስጥ በአስተባባሪነት ለሰሩት የላቀ አፈፃፀም ተሸላሚ በመሆን ዩኒቨርሲቲውን ያስጠሩ ተመራማሪ ሲሆኑ አይኤፍኤስ (IFS) በተባለ ፕሮጀክት ላይም በሥራ ትጋታቸው ሽልማት አግኝተዋል፡፡ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተደረገው የተመራማሪዎች ሽልማት ፕሮፌሰሩ በ2005 እና 2006 ዓ.ም የአመቱ ምርጥ ተመራማሪ በመሆን ተሻላሚ ነበሩ፡፡

ተመራማሪው ሙያቸው የሚፈቅደውን አገልግሎት ለመስጠት የተለያዩ የሙያ ማህበራት ውስጥ አባል በመሆን ሙያቸውን ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ በሙያቸው ለአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃ መምህራን በተለይ በሳይንስ ዘርፍ እውቀት በመገንባት ረገድ እንዲሁም የሙያ ማሻሻያ ዘዴ ላይ በማተኮር የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ከሙያ አጋሮቻቸው ጋር በመሆን አጫጭር ስልጠናዎችን ሰጥተዋል፡፡ ብዙ ተመራማሪዎችን ለማፍራት በሚደረገው ጥረት ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ረገድ ፕሮፌሰሩ ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ በማድረግ በተያዘው ተቋማዊ ለውጥ እያደረጉ ያለው ተግባር ከፍተኛ እንደሆነ የዩኒቨርሲቲው ሴኔት እና ቦርድ በማመን የማዕረግ እድገቱ እንደሰጠ ታውቋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ሴኔትና ቦርድ ለፕሮፌሰር ሙሉጌታ የማዕረግ እድገቱን ሲሰጥ የዩኒቨርሲቲውን የማዕረግ እድገት አሰጣጥ ፖሊሲ መስፈርትን አሟልተው በመገኘታቸው እንደሆነ ውሳኔው ያመለክታል፡፡ ፕሮፌሰር ሙሉጌታ በመማር ማስተማር፣ ችግሮችን በመመልከትና ለችግሮች መፍትሄ ለማምጣት በሚያደርጉት ያልተቋረጠ የምርምር ስራዎቻቸውን እንዲሁም የማህበረሰብ አገልግሎት የተሳትፎ ስራዎች በመገምገም ለዩኒቨርሲቲው የርዕይ ጥበብ 2017 ጉዞ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረጉና እያደረጉ ያሉ ተመራማሪ መሆናቸው የዩኒቨርሲቲው ሴኔትና ቦርድ ባደረገው ስብሰባ ገልጿል፡፡

## የስርዓተ ትምህርት ግምገማ ተካሄደ

በአበባ ሐብቱ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሳይንስ ኮሌጅ የስነ-ህይወት ት/ክፍል በአፕላይድ ማይክሮ ባዮሎጂ (Applied Microbiology) የሶስተኛ ዲግሪ ስርዓተ ትምህርት የሚገመግም አገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው የድህረ ምረቃ ዲን ዶ/ር አለማየሁ ቢሻው ስርዓተ ትምህርቱን በማዘጋጀት ለተሳተፉት ምሁራን ምስጋና ያቀረቡ ሲሆን የስርዓተ ትምህርቱ መከፈት የዩኒቨርሲቲው ራዕይ አንድ ስኬት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የሶስተኛ ዲግሪ ስርዓተ ትምህርቱን የቀረፁት የትምህርት ክፍሉ መምህር ፕሮፌሰር ሙሉጌታ ክብረት ስለ ስርዓተ ትምህርቱ ቀረጻ ሂደት እና ይዘት ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን ከአዲስ አበባ እና ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ምሁራን በቀረበው ማብራሪያ መነሻነት ልምዳቸውን በማካፈል ገንቢ የሆነ ሐሳባቸውንና አስተያታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ የባዮሎጂ ትምህርት ክፍል ዲንና መምህራን እንዲሁም የሚመለከታቸው ሀላፊዎች ተገኝተዋል፡፡

To follow the latest news about BDU, check out our website:- **http://www.bduinfo63@bdu.edu.et or http://www.bdu.edu.et**
facebook address:- **www.facebook.com/bduethiopia**

# መልዕክቶችና አስተያየቶች

## ርዕሰ-አንቀጽ

### ትውልዳዊ አደራችንን በፅናት በመወጣት ሀገራዊ ትልቅነታችንን እናረጋግጣለን!

አባቶቻችን በየጊዜው ሀገራችንን በቅኝ ግዛት መዳፋቸው ለማስገባት የቋመጡትን ወራሪዎች የዘመኑ አርበኞች ከያሉበት ተጠራርተው፣ ክንዳቸውን አበርትተውና በዓላማ ፀንተው መክተዋል። ብሔራዊ ማንነታቸውንና ክብራቸውን በተጋድሎአቸው ጠብቀው ከማዝለቅ ባለፈም ሀገራቸውን የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተምሳሌት አድርገዋል።

ከሀገራቸው ሉዓላዊነት፣ ከነፃነታቸውና ከማንነታቸው በላይ አንዳችም ነገር የማያስቀድሙት የሀገራችን ሕዝቦች ባላቸው የረጅም ዘመን የነፃነትና የተጋድሎ ታሪክ ዓለምን አስደምመዋል። በአድዋና በሌሎች ጦርነቶች ላይ በወራሪዎችና ፋሺሽቶች ላይ የተጐናፀፏቸው ድሎች የጥቁር ህዝቦች የነፃነት ተምሳሌቶች ሆነው የዘመናትን ድንበር ዘልቀዋል።

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አንድነት፣ የሀገር ተቆርቋሪነትና ለጠላት አይበገሬነት የቅርብ ሳይሆን የሩቅ ዘመን ታሪክ እንዳለው ከማንም የተሰወረ አይደለም። በነፃነት ወዳድነታቸውና የአንድነት ፅናታቸው ለዚህ አኩሪ ገድል የበቁት ኢትዮጵያዊያን መቼም ቢሆን በሀገራቸው ሉዓላዊነት ላይ የተደራደሩበት አጋጣሚ ተፈጥሮ አያውቅም። ኢትዮጵያዊያኑ ፀንቶ በዘለቀው አንድነታቸው የጋራ ጠላቶቻቸውን በጋራ የመመከት እና አሳፍሮ የመመለስ አኩሪ ባህል ቢኖራቸውም ለዘመናት እድገት እንቅፋት የሆነውን ርሀብና እርዳታ ጠባቂነት ለማስወገድ የተጓዙበት መንገድ ብዙም ሊያስኬዳቸው አልቻለም። በአባቶቻችን የፀናው የትግል አቋም ቅኝ አገዛዝን ላለመቀበል በፅናት እንደመቆማቸው የአሁኑም ትውልድ ለጋራ እድገታችንና ዘላቂ ተጠቃሚነታችንን በአንድነትና በቁርጠኝነት መስራት ይጠበቅብናል። በተሰማራበት መስክ ሰፊ የሆነውን የሀገሪቱ መሬትና ተዝቆ በማያልቀው የተፈጥሮ ሃብት በመጠቀም ርሃብን ድል መንሳትና ተረጂነትን ማስወገድ ከትውልዱ የሚጠበቅ ሀላፊነት ነው።

እኛ ኢትዮጵያውያን ነባሩን የተረጂነትና የድህነት መንፈስ በመቀየር ትኩረታችንን ወደልማትና እድገት እንዲያቀና በተለይ የተማረው ክፍል የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ሀገሪቷና ሕዝቦቿ ከድህነትና ኃላቀርነት መላቀቅና አንገታቸውን ማቅናት እንዳለባቸው ለማንም ግልጽ የሆነ ቢሆንም ወደ ተግባር በመግባት መንቀሳቀስ እጅጉን አስፈላጊ ነው።

የኢትዮጵያዊያን የአንድነታችን መተሳሰሪያና የእድገት ሂደታችን ዓይነተኛ መገለጫ ተደርጐ የተወሰደው የህዳሴው ግድብ ግንባታ በላቀ የአፈፃፀም ብቃት በሚቀጥለው ወር አራተኛ ዓመቱን ያከብራል። ይህ ታሪካዊ ክንውን ደግሞ የጥቁር ሕዝቦች የተጋድሎና የነፃነት ታሪክ ዓይነተኛ መገለጫ የሆነውንና በያዝነው ወር ማገባደጃ ላይ በመላ ሀገሪቱ በድምቀት የተከበረውን 119ኛው የአድዋ የነፃነት ድል በዓል የተለየ ያደርገዋል። ለሀገራዊ የልማትና እድገት ግስጋሴ መሰረት የሆነው የአድዋ ድል በዓል የኢትዮጵያ ሕዝቦች ቃል ኪዳናቸውን የሚያድሱበት፣ የሕዳሴ ጉዞአቸውን አፈፃፀም የቃኙበትና ለተሻለ አፈፃፀምና የጋራ ተጠቃሚነት ቁርጠኝነታቸውን የሚያረጋግጡበት መሆን አለበት። ዝክረ በዓሉ የሀገሪቱንና የሕዝቦቿን ትልቅነት ለመመለስ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን ባስገነዘበ መልኩ ተከናውኗል። የሁሉም የሀገሪቱ ዜጐች የነቃ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑ በዝክረ በዓሉ የተለያዩ መድረኮች አድንኦት ተሰጥቶታል።

በርካታ ምሁራንን ያፈራውና እያፈራ ያለው ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ታሪካዊ ሁነቶችንና ክንውኖችን በትክክለኛ መረጃ ላይ በመመርኮዝ ዝክረ በአሉን በማክበር የአሁኑ ትውልድ የሚጠበቅበትን አደራ በማሳወቅ ሀላፊነቱን መወጣት እንዳለበት ይታመናል። በዘርፉ የተሰማሩ ምሁራን በምርምር የተደገፈ እውቀቶችን በመተንተን፣ ትርጉም በመስጠትና እውነታውን በመለየት ለማህበረሰቡ ትክክለኛ መረጃዎችን ማድረስ ይጠበቅባቸዋል። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሀገራዊው የለውጥ ሽግግር ሂደት እውቀትን ማዕከል አድርጐ እንዲከናወንና ፍፃሜው የተሳካ እንዲሆን ያልተገደበ ተሳትፎአቸው ወሳኝነት አለው። የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብም ይህንን ሀላፊነት በመወጣት የሚጠበቅበትን ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ እናረጋግጣለን።

## ቁልፍ መልዕክት

### ዕውነትን የመፈለግ ጠቀሜታ በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ዕውነት ምንድን ናት? ዕውነት ትወለዳለችን? ዕውነት ታድጋለችን? ዕውነት ትሞታለችን? ወዘተ. ብሎ በመጠየቅ በርካታ ውይይቶች ሊካሄዱ ይችላሉ፡፡ በተለይ ሙስናን የሚፀየፉ፣ ሀቀኛ፣ ታታሪና ሀገር ወዳድ ዜጐች እንዲበራከቱባትና ህዳሴዋን እንዲያረጋጋጡላት ለምትፈልገው ኢትዮጵያችን ዕውነት መሠረታዊ ጉዳይ ናት፡፡ በመሆኑም ይህችን መሠረታዊ ሀሳብ ምንነቷንና በተግባር እንዴት እንደምትገለጽ የተሻለ ግንዛቤ መያዙ ጠቃሚ ነው፡፡ በዚህ ጽሑፍ ዕወነት በራዕይ ጥበበ 2017 እንዴት እንደምትገለጽና ስለ እሷ የተጠየቁትን ጥያቄዎች እንዴት እንደሚመለሱ በማቅረብ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ በጉዳዩ ላይ እንዲወያዩበት ለማነሳሳት እንሞክራለን፡፡

በራዕይ ጥበብ 2017 ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉ ዕውነቶችና በየቀኑ የሚወለዱ ዕውነቶች እንዳሉ ይታመናል፡፡ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ዕውነቶች የሚተላለፉበት መንገድ በቃልና በስነ-ጽሑፍ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የመተላለፍ ሂደት ዕውነቶች ላይ የመቀነስ፣ የመጨመርና የማዛባት ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ መገመት ቀላል ነው፡፡ ስለሆነም አሁን በስሜት ህዋሶቻችን ተጠቅመን እነዚህን የተላለፉልንን ዕውነቶች ስናይ ጥንቃቄ በተሞላበትና ጥልቅ ትንተና አድርገን ካልመዘንናቸው በስተቀር ዕውነትን ራሷን ሳይሆን የምናገኘው ሌሎች የቀነሷትን፣ የጨመሯትን ወይም ያዛቧትን ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ዕውነት አትገኝም፡፡ ስለሆነም በራዕይ ጥበብ 2017 ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉ ዕውነቶችን ስናይ በሚገባ ልንተነትናቸው፣ እርስ በርስ ያላቸውን ቁርኝት ልንቀምርና በተለያዩ ሁኔታዎች ልንመዝናቸውና በዚህ አግባብ ያጣራናቸውን አንፃራዊ ዕውነቶች በዕውነትነት ልንይዝ እንደሚገባ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

በየቀኑ የሚወለዱ ዕውነቶች ደግሞ እኛ የምንወልዳቸው፣ ሌሎች ሲወልዷቸው በአይናችን ያየናቸውና ሌሎች ደግሞ በወሬ ወይም በጽሑፍ መወለዳቸውን ያወቅናቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እኛ የምንወልዳቸው ዕውነቶች እንዴት ሊቀነሱ፣ ሊዛቡና ሊጨመሩ እንደሚችሉ በምሳሌ ማስረዳት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አንድ ኃላፊ ቢሮ እህቴን ወደዚህ መስሪያ ቤት አዙርልኝ ብለን ጠየቅን እንበል፡፡ ኃላፊውም የዝውውር ህጉን ጠቅሶ በዚህ ህግ መሠረት እንደማይቻል ገለፀ እንበል፡፡ በዚህ ሂደት የወለድነው ዕውነት "እኛ እህታችን እንድትዞር መጠየቃችንና ኃላፊውም ህጉ እንደማይፈቅድ መናገሩ" ከኃላፊው ቢሮ የተወለደ ዕውነተኛ ድርጊት ነው፡፡ የተወለደችዋ ዕውነት ይች ናት፡፡ ግን ወዲያው ከቢሮ እንደወጣን ለአንደኛው ጓደኛችን "አንተ ኃላፊው ቢኖ ሄጄ እህቴን አዙርልኝ ስለው አንተም መስሪያቤቱን እንድትለቅ እፈልጋለሁ እንኳን እህትህን ላዞርልህ አለኝ" ብለን ብንናገር ዕውነትን ለዚያውም እኛ የወለድናትን ዕውነት አዛባናት ማለት ነው፡፡ ለሌላኛው ጓደኛችን ደግሞ "አንተ ኃላፊው ቢሮ ሄጄ እህቴን አዙርልኝ ብለው እኔን በጣም እንደሚወደኝና እህቴም ብትመጣ በጣም እንደሚፈልግ ግን ህጉ እንደማይፈቅድ ነገረኝ" ብሎ ቢናገር ዕውነትና ጨመረባት ወይም ያልነበራትን ማጣፈጫ ጨመርንላት ማለት ነው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያልን የዚችን ዕውነት በጊዜ ብንከታተላት በጣም አድጋ፣ ተስፋፍታና በመሠረታዊ መልኩም ተዛብታ ልናገኛት እንችላለን፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥም ጠባቂና አስቀማጭ አጥታ ልትሞት ትችላለች፡፡ በጣም አሳዛኙ ጉዳይ ግን የጠበቀና ጥልቅ ትንተና ካልተደረገ በስተቀር ይቺ የተዛባች ነገር ለሚቀጥለው ትውልድም ልትተላለፍ መቻሏ ነው፡፡ ሌሎች ሲወልዱት ያየነውም ሆነ በቃል ወይም በስነ-ጽሑፍ ያገኘነው ነገር እንዲህ ልናዛባው እንችላለን፡፡ በተቃራኒውም በመሄድ ልናስተካክለውና የመጀመሪያ የተወለደችዋን ዕውነት ልናገኝ እንችላለን፡፡ በመሆኑም ለብዙ ጊዜ ተዛብታ የነበረችው ወይም ጠፍታ የነበረችው ዕውነት ልትገኝ ትችላለች ማለት ነው፡፡

ከነዚህ ዕውነታዎች በመነሳት ዕውነት የምትወለድ፣ ልታድግ፣ ልትዛባ፣ ልትሞትም የምትችልና ሞታም ልትነሣ የምትችል አስገራሚ ነገር ናት፡፡ በራዕይ ጥበብ 2017 ያስቀመጥነው አቅጣጫ ዕውነት ከተወለደች በኋላ ሳትዛባ፣ ሳትሞትና ሳትጠፋ እንድትኖር በማስቻል ሌሎች በርካታ ዕውነቶችን እንድትወልድና ከዚህ ቀደም የሞቱ ወይም የተዛቡ ዕውነቶች ካሉ ከሞት በማስነሳትና በማስተካከል ዕውነቶች የዕውቀት መሠረት እንዲሆኑ ለማድረግ ነው፡፡ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብም ይህን ዕውነትን የመፈለግ ጥማት ይዞ በመረባረብ እርስ በርሱ የሚፈቃቀርና የሚደጋገፍ ማህበረሰብ በመሆን ዩኒቨርሲቲያችን ታላቅ ተቋም ማድረግ ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን እንደ ዕውነት ውሸትም ትወለዳለች፣ ታድጋለች፣ ትዛባላች፣ ትሞታለች፣ ሞታ ትነሳለች፡፡

ዕውነትና ዕውነት ብቻዋን የዕውቀታችንና ፍርድ የመስጫ መሰረታችን እንድትሆን ሌት ተቀን ለምትሠሩ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ያለን አድናቆት ታላቅ ነው፡፡ በምሳሌነታችሁ እንወዳችኋለን፡፡ እናከብራችኋለን፡፡ ምንጊዜም ዕውነትን ስለምታራምዱ ለራዕይ ጥበብ 2017 ስኬት መሠረቶች ናችሁ፡፡ ሁላችንም የነዚህን ብርቅዬ የዩኒቨርሲቲያችን ሠራተኞች ፈር ተከትለን የዕውነትን መስመር እናጠንክር፡፡ ሁሉም ሀይማኖቶቻችንም የሚሰብኩት ዕውነትን ነውና ዕውነትን መከተል

ለራሳችንም ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው፡፡

**ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!!!**

# አበይት ዜናዎች...

## አገር አቀፍ አውደ ጥናት ተካሄደ

በየማነ ገብሩ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ በአሜሪካና በካናዳ መንግስታት ከሚደገፍው ሴፍ (SAFE - Sasakawa, African fund for extension education program) አጋር ድርጅት ጋር በመተባበር ለ2ተኛ ጊዜ በ mid career agricultural extension መርሃ ግብር ለሁለት ዓመት ከስድስት ወራት በቅድመ ምረቃ ያሰለጠናቸውን ተመራቂ ተማሪዎች የተግባር ተኮር የመመረቂያ ጽሑፍ (የምርምር ግኝት) የሚገመግም አገር አቀፍ አውደ ጥናት አካሄደ።

ዓውደ ጥናቱን በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የከፈቱት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ በአሁኑ ጊዜ በኢኮኖሚ ያደጉ የአለማችን ሀያል ሀገራት የዕድገት ምስጢር የምርምር ተቋማቸውና ዩኒቨርሲቲዎቻቸው በቴክኖሎጅ፣ በጤና፣ በሳይንስና በትምህርት ዘርፍ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ የምርምር ውጤቶችን ማበርከት መቻላቸውንና ጠንካራ የእርስ በርስ ግንኙነት መፍጠር በመቻላቸው መሆኑን ጠቁመው በአፍሪካ የሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ከዚህ ልምድ በመነሳት ግንኙነትታቸውን በማጠናከር የሰለጠነ የሰው ሀይል ማፍራት ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት እንዳለባቸው መልዕክት አስተላልፈዋል።

የግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር በላይነህ አያሌው የአውደ ጥናቱን መሰረታዊ አላማዎችን ሲገልጹ ተመራቂ ተማሪዎች በየአካባቢያቸው የሚታዩ የአርሶ አደሩን ነባራዊ ችግሮችን በመለየትና ያገኙትን የምርምር ውጤቶች ማስገምገምና ሌሎች ተማሪዎች ከተመራቂ ተማሪዎች ልምድ በመውሰድ በጽንሰ ሃሳብ የተማሩትን ትምህርት በተግባር በመደገፍ ለምረቃ የሚያበቃቸው የምርምር ስራዎችን እንዲያቀርቡ የሚያግዝ ነው።

የአማራ ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ ዶ/ር ተሾመ ዋለ በክልሉ ውስጥ የሚታየውን የሰለጠነ የሰው ሀይል ክፍተት ለመሙላት ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከቢሮው ጋር በመተባበር በሙያቸው ጥሩ የሥራ አፈፃፀም ላሳዩ የግብርና ኤክስቴሽን ባለሙያዎች ሙሉ ወጭያቸውን በመሸፈን በዲግሪ ደረጃ እያሰለጠነ መሆኑን አድንቀው ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል።

ለሶስት ተከታታይ ቀናት በተካሄደው አውደ ጥናት ላይ ከሀረማያ፣ ጅማ፣ ሐዋሳና ወሎ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲሁም ከውጭ አገር ከቤኒ፣ ኡጋንዳ፣ ጋና፣ ናይጄርያና ማላዊ ዩኒቨርሲቲዎች ምሁራን ተሳትፈዋል።

## ዩኒቨርሲቲው የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረመ

በአበባ ሐብቱ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲና አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በጋራ ለመስራት የሚያስችላቸውን ስምምነት ተፈራረሙ። ስምምነቱን የዩኒቨርሲቲው የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድና የአብክመ የመ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር የተከበሩት አቶ ንጉስ ጥላሁን ተፈራረመዋል።

በሁለቱ ተቋማት መካከል የታቀደውን የመደጋገፍና ትብብር ስራ አስመልክቶ የመግቢያ ንግግር ያደረጉት የጽ/ቤቱ ም/ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ ፀጋዬ በቀለ ስምምነቱ ለጽ/ቤታቸው የመጀመሪያ የሆነና ጽ/ቤቱ ምሁራንን በማፍራት ልምድ ካለው ዩኒቨርሲቲ ጋር ለመስራት መፈራረሙ ክልሉን በኮሚኒኬሽንና መረጃ ዘርፍ ወደ አንድ ከፍታ የሚያሳድግ መሰረት ነው ብለዋል።

የአብክመ የመ/ከ/ጉ/ጽ/ቤት ዋና ዳይሬክተር የተከበሩ አቶ ንጉስ ጥላሁን የድጋፍ ስምምነቱን በኢንፎርሜሽን የክልሉን የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ዘርፍ በእውቀትና በሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን ከዩኒቨርሲቲው ጋር በጋራ መስራት ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

ዶ/ር ፍቅረ ሰላም በበኩላቸው ዩኒቨርሲቲው በክልሉ ብቻ ሳይሆን በሃገሪቱ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ተቋም እንደሆነ ገልጸው በሀገር ውስጥ ብቻ ሳይወሰን ከአፍሪካ ካሉ 10 የምርምር ተቋማት አንዱ ለመሆን እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል። ስምምነቱን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ሁለቱም ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ሀላፊነት መወጣት እንዳለባቸው አሳስበዋል።

በፊርማው ስነስርዓት ላይ የአብክመ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት ባለሙያዎች፣ የሚመለከታቸው የመንግስት ሀላፊዎች እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው መምህራን ተገኝተዋል።

## ለጉብኚዎች ገለጻ ተሰጠ

በሙሉጉጃም አንዱአለም

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን፣ ሠራተኞችና በውጤታቸው ከፍተኛ ነጥብ ያስመዘገቡ ተማሪዎች በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ትምህርታዊና ልማታዊ ጉብኝት አካሄዱ።

ለጎብኚዎቹ መግለጫ የሰጡት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ የዩኒቨርሲቲውን ራዕይና ተልዕኮ በማብራራት ሀገሪቱን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የምታደርገውን ጥረት ዩኒቨርሲቲው የሚጠበቅበትን ለመወጣት ከመማር ማስተማር፣ ከመመራመር እንዲሁም ማህበረሰቡን ከማገልገል ጐን ለጐን ሀብትን ከማፍራት አኳያ ጠንክሮ እየሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

ፕሬዚዳንቱ አያይዘው ተቋሙን ከማስፋፋት አኳያ በመገንባት ላይ ያሉ ተጨማሪ ግቢዎችን በስዕላዊ መግለጫ ያስተዋወቁ ሲሆን የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግና ብቁ ባለሙያዎችን ከማፍራት አንጻር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የረጅም ጊዜ ግንኙነት እንዳላቸው ጠቁመው ለወደፊትም ትስስሩ ተጠናክሮ እንዲቀጥልና የበለጠ ስራ መሰራት እንዳለበት አስገንዝበዋል።

ጎብኚዎቹ በበኩላቸው እንደገለፁት ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በርካታ የሀገር ኩራት የሆኑ አመርቂ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑን በጉብኝታቸው ወቅት መገንዘባቸውን ተናግረዋል።

## ተቋሙ ከባለሙያዎች ጋር ምክክር አካሄደ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም በተቋሙ ምስረታና አሰራር ላይ ያተኮረ የባለሙያዎች ምክክር አካሄደ። በምክክሩ ላይ ምሁራን በአማርኛ ቋንቋ እድገትና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዩች ዙሪያ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር ፕሮፌሰር ባየህ ይማም የቋንቋ ብልፀጋ (Lexical Development) በሚል ርዕስ ፅሁፍ ያቀረቡ ሲሆን በፅሁፋቸው ቋንቋ የሚወድቅ፣ የሚነሳ፣ የሚሞት፣ የሚድንና የሚያድግ መሆኑን ገልጸው ለአፍ የሚቀል አጭርና ለጊዜው አዲስ የሚመስል ግን የሚለመድ ከትርጉሙ ብዙ ያልራቀ ቃል በመጠቀም ቋንቋን ማሳደግ እንደሚቻል ጠቁመዋል። አያይዘውም የዩኒቨርሲቲው የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም ቋንቋን ከማሳደግ አኳያ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበት ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ታሪክና ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረጉት እና በማሕበራዊ ሚዲያዎች ላይ የተለያዩ ፅሁፎችን የሚፅፉት ዲያቆን ዳንኤል ክብረትም የአማርኛ ቋንቋ ከየት ወዴት - ተግዳሮቶቹና መፍትሄዎቹ የሚል ፅሁፍ አቅርበዋል። በፅሁፋቸውም የአማርኛን ቋንቋ ጉዞ በአምስት ምዕራፍ ማለትም ከጥንት - 13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ ከ13ኛ ክፍለ ዘመን - 16ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን - ዘመነ ቴዎድሮስ፤ ከዘመነ ቴዎድሮስ - ዘመነ ምኒሊክና ከዘመነ ምኒሊክ - አሁን በመክፈል አብራርተዋል። አማርኛ በየትኛው ዘመንና በእነማን እንደተጀመረ ተጨባጭ የሆነ መረጃ እንደሌለው ጠቅሰው በተለይ ከጥንት እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ያለው ቋንቋ አመጣጥ ተጨባጭ መረጃ ሊገኝ ባለመቻሉ በሚገባ ሊታወቅ አልቻለም ብለዋል። ተቋሙም በምርምር የተደገፈ መረጃን በመሰብሰብ ለህብረተሰቡ ለማድረስ ሚናው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸዋል።

የአማርኛ ቋንቋ እድገትና ቋንቋውን እንዴት ማሳደግ ይቻላል በሚል ርዕስ ላይ ፅሁፍ የቀረበ ሲሆን ከተሳታፊዎች ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጎበታል። በእለቱ ከአማርኛ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ፣ ከእንግሊዝኛ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ፣ ከባህል ጥናት (ፎክሎር) እንዲሁም ከጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ት/ክፍሎች መምህራን ተሳትፈዋል። ዩኒቨርሲቲው በአማርኛ ቋንቋ ላይ የሚደረጉ የምርምር ውጤቶችን መሰረት በማድረግ በቋንቋው ላይ የሚታየውን ችግር በተግባር ለመፍታት እንዲቻል በማሰብ የአማርኛ ቋንቋ ማበልፀጊያ ተቋም መመስረቱ ይታወሳል።

ዜናዎቻችንን በድረ-ገጻችን **http://www.bduinfo63@bdu.edu.et** ወይም http://www.bdu.edu.et እና በፌስቡክ ገጻችን www.facebook.com/bduethiopia መከታተል ይችላሉ።

# ሯጩ

በሂሩት አድማሱ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት

nanihira@gmail.com

ወደ ቀጠሮ ቦታዬ ለመድረስ ያለችኝ ደቂቃ ትንሽ ናት። ልብ እየቸኮለ እግር እየዘገየ ከማስቸገሩ በተጨማሪ የምሰራበት መስሪያ ቤት ግቢን ለቆ ባጃጅ ለመያዝ እስከበር ድረስ የተዘረጋውን አስፋልት በእግር መጓዝ ግድ ስለሚያስፈልግ በቶሎ መድረሴ አጠራጣሪ ሆኖብኛል። በርግጥ የምሰራበት መስሪያ ቤት በተሽከርካሪ ሃብቱ በከተማው የሚመጣጠነው እንደሌለ እገምታለሁ። ይሁንና እስር ግዜ ውር ውር ከሚሉት መኪኖች ባንዱ ለመሳፈር ወይ ባለስልጣን መሆን አሊያም በሹፌሮች ጋር የጠበቀ ትውውቅ ያስፈልጋል። እዚህ ላይ እንደ ቀልድ የሚተረበው ተረብ ትዝ አለኝ። ተረቡ አንዳንድ የፔዳ ሹፌሮች ‹‹መምህር ከመጫን ይልቅ ገጭቶ ማለፍ ይቀላቸዋል›› የሚል ነው። ወደ ጉዳዬ ስገባ ያለችን የተጣበበች ሰዓት አብቃቅቼ መልዕክቴን ለመቀበል ሩጫ አይሉት እርምጃ ቅጥ እየተጣደፍኩ ስጓዝ የሚያውቀኝን ሹፌር አገኘሁና ፈጣሪን እያመሰገንኩ ተሳፈርኩ።

ረጅሙን የግቢ መንገድ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ተገላገልኩ። የዋናውን ግቢ በር ለማለፍ ግን ፍተሻ ግድ ነበር። እሱንም ተገላገልን። የሚገርመው ግን መኪኖች ለፍተሻ እንዲቆሙ የሚያግደው ወፍራም ገመድ መሬት ላይ ባለመውረዱ መጓዝ አልቻልንም። የሁሉንም ትኩረት የሳበ አንዳች ነገር ተከስቶ እኛ በመኪናው ውስጥ እንደተጎለትን ቀረን። በእግሬ ወርጄ ለመሄድ አምሮኝ ካሁን አሁን ገመዱ ወርዶ እንሄዳለን በሚል ተስፋ ጋቢና ቁጭ ብዬ መቁነጥነጤን ቀጠልኩ። ዓይኖቼን የሰውን ሁሉ ትኩረት ወደ ሳበው ግርግር ወረወርኩ። ግርግሩና ትኩረት የሳበው ጉዳይ አንድ ተማሪ መሰል እንግዳ በመታወቂያ አሳይ አላሳይም ሰበብ ከግቢው የጸጥታ ሰራተኛ ጋር ንትርክ ውስጥ በመግባቱ የተፈጠረ ነው። የተፈጠረው ችግር በቀላሉ የሚፈታ ቢሆንም የሁሉም የጸጥታ ሌላውን ቸል ማለትና በዚህች አንድ ችግር ላይ የተሰጠው ትኩረትና የስራ ላይ ቸልታ ለሞት የሚያጣጥር በሽተኛ ይዘን ቢሆንም ይሰናበታታል እንጂ ማን ተባብሮት ያሰኛል። ግር ግር የፈጠረው ተማሪ መሰል እንግዳ በሶስት የጸጥታ ሰራተኞች ታጅቦ ወደ እኛ መኪና ቀረበ። «ሹፌር ተባበረን ፖሊስ ጣቢያ አድርሰን።» አለ አንዱ የጸጥታ ሰራተኛ።

«ምን ችግር ተፈጠረ?» አልን ሁላችንም ለነገሩ ጓጉተን።

> ወደፖሊስ ጣቢያ የሚሄዱ ነገር ቁርጥ ሲሆን የመኪናው አቅጣጫ ተቀየረ። ይህ ደግሞ የኔን መንገድ ያረዝማል እንጂ ያለችኝን ደቂቃ አይቆጥብልኝም።

በመታወቂያ አሳይ አላሳይም፤ እገባለሁ አትገባም ክርክር ወደ አካላዊ ጠብ ያመሩት የጸጥታ ሰራተኛዋና ተማሪ መሰል እንግዳው እኩል ማውራት ጀመሩ።

«ህግ የሌለበት አገር የምትኖር መሰለህ እንዴ ተገፋትረህና ጉዳት አድርሰህብኝ የምትሄደው?» አለች ገፍትሯት ሊገባ ሲል ከግድግዳ ጋር በመፋተጓ የተላጠውን እጇን በቁጭት እየተመለከተች።

«አጥፍቻለሁ ይቅርታ አድርጊልኝ።» አላት። ብዙ የይቅርታ ቃላትን እያወጣ ተማጸናት። ጨርሳ ልትሰማው አልወደደችም። በመኪናው ውስጥ ያለነው ግማሻችን ወደጉዳያችን ፈጥነን ለመድረስ ሌሎቻችን ደግሞ የልጁ ይቅርታ አጠያየቅ አሳዝኖን ይቅርታ እንድታደርግለት ለመናት። አልሰማችንም፤ ልትሰማንም አልፈለገችም።

ወደፖሊስ ጣቢያ የሚሄዱ ነገር ቁርጥ ሲሆን የመኪናው አቅጣጫ ተቀየረ። ይህ ደግሞ የኔን መንገድ ያረዝማል እንጂ ያለችኝን ደቂቃ አይቆጥብልኝም። ያለኝ አማራጭ ሹፌሩን ይቅርታ ጠይቄ አዲሱ የአስተዳደር ህንጻ የሆነው ጥበብ ህንጻ ጋር መውረድ ነበር። እኛም ጥበብ ሕንጻ ጋር እንዲያወርደኝ ሹፌሩን ጠየኩና ወረድኩ። በጣም ተጨናንቀው ኗላ ተቀምጠው ከነበሩት የጸጥታ ሰራተኞች አንዱ እኔ ወደ ወረድኩበት ጋቢና ሊገባ በደስታ እያመራ እያለ ሊከሰስ ወደ ጣቢያ ተይዞ ይሄድ የነበረው ልጅም ወርዶ ሩጫውን ጀመረ። በሁኔታው የተደናገጡት የጸጥታ ሠራተኞች ቆመው ከመመልከት መከተልን መረጡ። አትታዘቡኝ የልጁ ፍጥነት የአጭር ርቀት ሩጫ ተወዳዳሪ አይነት ሆኖ ለውድድር እንጂ ለማምለጥ የሚሞክር አይመስልም ነበር። ተከትለውት የሚሮጡት ደግሞ ለአድናቆት የሚከተሉት ሆኖም ያልደረሱበት ይመስላሉ። ለሯጩ አድናቆቴን ቸርኩት። ተክለሰውነቱ አሯሯጡ ሁሉ የአትሌት እንጂ መታሰርን ፈርቶ የሚሸሽ አላስመሰለውም።

በሩጫ ሲከተሉት የነበሩት የጸጥታ ሰራተኞች መኪና እንዳለ ትዝ ሲላቸው ወደ መኪናዋ እንደገና በመሮጥ ‹‹ተከተለው!›› አሉት። ሹፌሩ ድንገት ደርሰው አዛዥ በሆኑበት የጸጥታ ሰራተኞች ሁኔታ ቢገረምም ህገ ወጥ ሰውን ላለመተባበር ተከተለው። ጉዳዩ ‹ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ› ሆነና መኪና በማይገባበት አቋራጭ መንገድ ውስጥ ገብቶ ተሰወረ። በልጁ ስራ እጅግ የተናደደችው ይቅርታ ለመቀበል ያልፈቀደችው የጸጥታ ሰራተኛና ለመሄድ ከቸኮልኩበት ሳልደርስ በትዕይንቱ ተገርሜ የተገተርኩት እኔ በመዘግየቴ ምክንያት ሀሳባችንን ሳናሳካ ወደ ግቢ ተመለስን።

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል። እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን።

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በአድራሻችንና በኢሜል መላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን።

ዝግጅት ክፍሉ

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከጥር ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ

ባለፈው ዕትም …. ተማሪ ተስፋሁን በገጠመው ተደጋጋሚ ገጠመኞች - የምግብ ካርዱ እና የተማሪነት መታወቂያው መጥፋት - የተነሣ ግራ በመጋባት እንደገና ለማግኘት ክሊራንስ እያስፈረመ ጎን ለጎን ቸል ብሎት የቆየውን ትምህርት ጠንክሮ ለመከታተል በመወሰን ክፍል ገብቶ በመማር ላይ እንዳለ ሳያስበው በፖሊስ ተፈልጎ በተጠረጠረበት ወንጀል ክስ ተመስርቶበት በቁጥጥር ሥር ውሏል፡፡ በዚህም መሠረት በቁጥጥር ሥር ከዋለ በኋላ በፖሊስ ጣቢያው ያለውን ሁኔታ በመቃኘት ጭንቀት ውስጥ የገባ ቢሆንም ሌሎች በቁጥጥር ሥር የዋሉት እንደሱ የተጨነቁ ስላልመሰለው እንደገና በአዕምሮው ውስጥ ሌላ ጥያቄ አጭሮበታል፡፡ ቀጣዩ እጣ ፈንታው ምን እንደሚሆን ተከታዩን እንሆ……..

እኔ ከገባሁ ትንሽ ቆየት ብሎ ሌላ እሥረኛ መጣ፡፡ ወዲያው በሩ ተከፍቶ እንደገባ የተወሰኑት አጨበጨቡለት፡፡ እሱም እጆቹን ወደ ላይ አንስቶ ‹‹አብሽሩ! አብሽሩ!›› አለና ወደ ፊት በመሄድ ከአንዱ እሥረኛ ላይ እንደ ሰከረ ሰው ዘፍ አለበት፡፡ ከዚያም ‹‹የመብራት ገንዘብ በሀይለኛው ስለተዘጋጀ ማንም እንዳይነካኝ›› የሚል ማስጠንቀቂያ አዘል ማሳሰቢያ ሲሰጥ በድጋሜ አጨበጨቡለት፡፡ እኔም ነገሩ ግራ ስላጋባኝ እንዴት ነው? የማየው ነገር ሁሉ በእውኔ ነው ወይንስ በህልሜ? ፖሊሱ ሲነግረኝ ማረፊያ ቤት ትቆያለህ ነበር ያለኝ፡፡ ነገር ግን እንኳን ማረፊያ ሊሆነኝ ፅድቁስ ቀርቶ በቅጡ በኮነነኝ የሚያሰኝ ነገር ሆኖ ነው ያገኘሁት፡፡ መቆዘም ጀመርሁ፡፡

ሁሉም እሥረኛ እርስ በእርስ ያወራል፡፡ እኔ ግን ልቆጣጠረው በማልችለው ሁኔታ ስለተበሣጨሁ ከማንም ጋር ለማውራት አልፈለግሁም፡፡ ሌሎች የሚያወሩትንም ለመስማት ፍላጎትም የለኝም፡፡ ብቻ በተፈጠረው አጋጣሚ እየደረሰብኝ ያለውን መንገላታት ሣስበው የበለጠ እናደዳለሁ፡፡ ምክንያቱም ትምህርቴን ለመማር የረጅም ጊዜ ዓላማዬን ሰንቄ የእናቴን አደራ ተቀብዬ በሞራል የጀመርሁትን ትምህርት በዚህ መታወቂያ የተነሣ እንደ በግ ተጎትቼ እስር ቤት በመግባቴ የተለያዩ ሀሳቦች እየተደራረቡ ይመጡብኛል፡፡ ትንሽ ሣስብ ቆየሁና ወይኔ ቶኪቻው! ሻሼ እኮ ‹‹አርፈህ ትምህርትህን ተማር በዚች ልጅ የተነሣ ያልታሰበ ችግር ሊገጥመህ ይችላል›› ብላኝ ነበር፡፡ እኔ ነኝ አርፌ አልቀመጥ ብዬ…………

እርግጥ ነው፡፡ ለዚህ ሁሉ ችግር የዳረገችኝ ሔርሜላ ናት አልሁና መልሼ እሷን መውቀሱ ደግሞ ከበደኝ፡፡ ለነገሩማ እሷ ምን ታድርግ ለችግር የጣለኝ መታወቂያዬ ነው፡፡ መጀመሪያም ጠፍቶ በእሷ እጅ ገባ እሷ ይዛው ስትመጣ የሆነ የፍቅር ምትሃት ይዞብኝ መጣ፡፡ ይኸው አሁን ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ ጠፉና በፖሊስ እጅ ገብቶ ለእሥር ዳረገኝ፤ ከቶውንም ሌባ የሚል ስያሜ አሰጠኝ አልሁና ወይኔ በማለት ሣላስበው በንዴት ግንባሬን በመዳፌ ደጋግሜ ስደበድበው ከአጠገቤ ያለው እሥረኛ ‹‹ምነው? ወንድም አትናደድ እንጅ፡፡ ነገር እንደሆነ ከልኩ አያልፍም›› አለኝ፡፡ እኔም ዘወር ብዬ አየሁትና ዝም አልኩት፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ከቀኑ ስምንት ሰዓት አካባቢ ሲሆን ጠባቂው ፖሊስ በሩን በመጠኑ ከፈተና ‹‹ተስፋሁን የምትባል ትጠራለህ፡፡›› ሲለኝ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ስወጣ እነሣጅን ናቸው፡፡ እኔም ከበሩ እንደወጣሁ ወደ እነሱ ቀርቤ ሰላምታ ልለዋወጥ ሣመራ ‹‹በቃ! ከዚህ ማለፍ ክልክል ነው፡፡›› በማለት ፖሊሱ እኔንም እነሱንም አስጠነቀቀን፡፡ በዚህም ምክንያት እነሱም እኔም በሩቁ ባለንበት ቆምንና ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ከዚያም ሣጅን ወደ ፖሊሱ በመጠጋት ያወራው ጀመር፡፡ ሲያወሩ ከአሁን በፊት አብረው የቆዩ ጓደኞሞች ይመስላሉ፡፡ ትንሽ ቆየት ብሎ ፖሊሱ ወደ እሱ እንድጠጋ በምልክት አሣዬኝ፡፡

የፖሊሱን ፈቃድ እንዳገኜሁ ከሣጅን ጋር በመተቃቀፍ ሰላምታ ተለዋወጥን፡፡ ሌሎች ግን ፖሊሱን ስለፈሩ ይመስላል ራቅ ብለው እንደቆሙ እጃቸውን እያነሱ በድጋሜ ሰላምታ አቀረቡልኝ፡፡ ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ‹‹የታሰርክበት ምክንያት ምንድን ነው?›› በማለት ሣጅን ጠየቀኝ፡፡ እኔም ‹‹ፖሊሱ እንደነገረኝ ከሆነ አንድ ሱፐር ማርኬት በመዘረፉ በስርቆት ወንጀል ተጠርጥሬ እንደሆነ ነግሮኛል ደግሞ እንደ ማስረጃ ያቀረበው በተዘረፈው ሱፐር ማርኬት ውስጥ መታወቂያዬ መገኘቱን ነው፡፡›› በማለት ስነግረው በጣም አዘነ፡፡ ይህን ስንነጋገር አጠገባችን ያለው ፖሊስ ‹‹እንደዚህ ዓይነት ወሬ አሁን አይወራም እኔ እኮ እንድትቀራረቡ ያደረግሁት መረጃ ለማጥፋት የሚሆን ሀሳብ እንድትለዋወጡ ሳይሆን ምን አልባት እዚህ ስለታሠረ መቼም ስሜት ውስጥ በመግባት አዕምሮው እንዳይጎዳ የምታረጋጋው መስሎኝ ነው፡፡›› ሲል ሣጅን ፈጠን ብሎ ‹‹እሽ! እሽ! ችግር የለም፡፡ ሌላ ሌላውን እናወራለን፡፡›› አለና በመቀጠል ‹‹ለመሆኑ ምሣ በልተሃል?›› ብሎ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ‹‹ስለተበሣጨሁ ይመስለኛል ምንም ምግብ አላሰኘኝም፡፡ ደግሞ ይገርምሃል! እንደገባሁ የመብራት ብለው ደበደቡኝ፡፡ በዚህም ምክንያትና በሁኔታዎች አጋጣሚ ስለተናደድሁ እስከ አሁን ከማንም ጋር የሀሳብ ልውውጥ አላደረግሁም፡፡›› በማለት ብሶቴን አወራሁት፡፡ ሣጅንም ሲያዳምጠኝ ቆይቶ ‹‹ልክ አይደለህም፡፡ አብረውህ ካሉት እሥረኞች ጋር መመሣሰል አለብህ ያለዚያማ ብቸኝነቱን አትችለውም፡፡›› ሲለኝ ‹‹እንዴ! ምን ማለትህ ነው? እዚህ የተሰባሰቡት ሁሉ ምንም የሰው ልጅ ባህሪ ያላቸው አይመስሉኝም፡፡ እና ከእነሱ ጋር እንዴት መመሣሰል እችላለሁ?›› በማለት ስመልስለት ‹‹ልክ ነህ፡፡ እንደምትለው በሀሳብ ላትመሣሰሉ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ከእነሱ ልትማራቸውና ልታውቃቸው

‹‹ልክ ነህ፡፡ እንደምትለው በሀሳብ ላትመሣሰሉ ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ከእነሱ ልትማራቸውና ልታውቃቸው የሚገቡህ መረጃዎች ስለሚኖሩ ሀሳብህን በመቀየር ለመዋሃድ ሞክር …

የሚገቡህ መረጃዎች ስለሚኖሩ ሀሳብህን በመቀየር ለመዋሃድ ሞክር፡፡ ደግሞስ የመብራት መጠየቅ የተለመደ ነገር ነው፡፡ አንተ ስላልገባህ ነው እንጅ›› አለና ‹‹ለምንም ለምንም ለጊዜው ይህን ብር እንካ›› አለና የ50 ብር ኖት ሲሰጠኝ እንባዬ መጣ፡፡በዚህ ሁኔታ እንዳለሁ ፖሊሱ ‹‹በቃ ብዙ ጊዜ ስለቆያችሁ ወደ ውስጥ ግባ!›› በማለቱ ስሜት ውስጥ እንዳለሁ ተሰናብቻቸው ገባሁ፡፡

እንደገባሁ ‹‹ሣጅን ብቸኛ አትሁን በተቻለህ እዚያው ካሉት ጋር ለመግባባት ሞክር›› ያለኝን ሀሳብ ሳወጣ ሳወርድ ትንሽ ቆዬሁና አጠገቤ የተቀመጠውን ‹‹እሥረኛ አሁን ገንዘብ መጥቶልኛል፡፡ ለመሆኑ የሀምሣ ብር ዝርዝር ይኖራቸው ከሆነ ተሣቅቄ ከምሞት ያለብኝን ሦስት ብር ከፍዬ ብገላገል ይሻለኛል፡፡›› ስለው ቀስ ብሎ ጎሽም አደረገኝ፡፡ እኔም ወደ እሱ ጠጋ ብዬ ጆሮዬን ሰጠሁት፡፡ ‹‹የምን ክፍያ ነው? የመብራት ክፍያውን ከሆነ ቅድም አልፏል፡፡ ምክንያቱም በውል የተበደርኸው ዕዳ አይደለም፡፡ ያው እዚህ ያሉ ጋጥ ወጦች የፈጠሩት እንጅ በሕግ የተቀመጠ ጉዳይ ስላለሆነ አርፈህ ተቀመጥ፡፡ ከአሁን በኋላ ማንም የሚጠይቅህ የለም፡፡ ይልቅስ አዕምሮህን አታስጨንቅ፡፡ በተቻለህ መጠን አሁን የተከሰተብህን ችግር ለመርሣት ሞክር፡፡›› አለኝ፡፡ እኔም ‹‹እንዴት አድርጌ ልርሣው ያልታሰበ ዱብ ዕዳ፡፡ ሱፐር ማርኬት ዘርፈሃል ተብዬ ለእሥር ስዳረግ መናደድ ይነሰኝ እንዴ! አጋጣሚ ጠፍቶ ነው እንጅ ነገሩ እኮ ራስን እስከ ማጥፋት የሚያደርስ ጉዳይ ነው›› አልሁት፡፡ እሱም መለሰና ‹‹እንዴት! ነው? መቼም ፖሊስ መረጃ ሣይዝ ወይም የሆነ ፍንጭ ሣያገኝ አንተን ሌባ የሚልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ስለዚህ ከድርጊቱ ነፃ ከሆንክ ምርመራ ሲደረግልህ ሁኔታውን ማስረዳት ነው፡፡ ያለዚያም አድርገኸው ከሆነም መረጃ ቀርቦ ይረጋገጥብህ እንጅ ማመን የለብህም፡፡›› በማለት መከረኝ፡፡ ቆየት ብሎም ስለማንነቴ ጠይቆኝ ስነግረው በመገረም ይመለከተኝ ጀመር፡፡ እኔም በጥሞና ሳዳምጠው ቆየሁና ‹‹ፖሊስ እንደ መረጃ ያቀረበው መታወቂያዬ በተዘረፈው ሱፐር ማርኬት ውስጥ መገኘቱን ነው፡፡ መታወቂያዬ ደግሞ ቀደም ሲል በሌቦች ተሰርቆብኝ ነበር፡፡ ይህንንም ለማስረዳት ስሞክር ፖሊሱ በጭራሽ ሊቀበለኝ አልቻለም፡፡ እንዲያውም ዘና ብሎ ‹ይህ የፈጠራ ወሬ ነው፡፡› በማለት የበለጠ አናደደኝ፡፡›› አልሁና በዝርዝር ሳስረዳው በቃ አሁን ዝም በል በዚህ ሱፐር ማርኬት መዘረፍ የተነሣ ዛሬ ጠዋት ብዙ ተጠርጣሪ ሌቦች ስለገቡ በምርመራ ወቅት ለፖሊስ የማይናገሩትን ሚስጢር እዚህ ለጓደኞቻቸው ሊናገሩ ስለሚችሉ አሁን አንተ መታወቂያዬ እዚያ ተገኝቶብኝ ነው የሚለውን ተውና በምን ምክንያት ታሰርህ ቢሉህ ከሰው ጋር ተጣልቼ በመደባደቤ ነው በላቸው፡፡ እና ድርጊቱን ካልፈፀምክ መታወቂያህ እዚያ በመገኘቱ ብቻ ሰርቋል ተብሎ ድምዳሜ ላይ አይደረስም፡፡ ስለዚህ ስለተዘረፈው ሱፐር ማርኬት እዚህ ያሉ ሌቦች ሊያውቁ ስለሚችሉ ተረጋጋ፡፡›› አለና የሆነ የተስፋ ጭላንጭል አጫረብኝ፡፡ እኔም ‹‹ታዲያ ይህንን እንዴት ማወቅ እችላለሁ?›› በማለት ያለኝን ጉጉት ገለፅኩለት፡፡ እሱም ‹‹ችግር የለም አሁን መሸት ሲል ካሁን በፊት የሠሩትን እንደ ጀብዱ ስለሚናገሩ ዝም ብለህ ማዳመጥ ነው፡፡›› አለና የበለጠ ተስፋ ሰጠኝ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ ፖሊሱ ጠራኝና ስወጣ ሣጅን በፌስታል የሆነ ነገር ይዞ ከፊት ለፊት ቆሟል፡፡ ከዚያም ሊሰጠኝ ሲል ፖሊሱ እንዲያሳየው ጠየቀውና ከፌስታሉ ውስጥ በሣህን የታሰረ ምግብ ሲያወጣ ፖሊሱ ሣጅንን ፌስታሉን አስዘረጋውና በዚያ ላይ አስገለበጠው፡፡ ከዚያም መሐሉን በቢላዋ ከሁለት በመክፈል ካየ በኋላ እንዲቀምሰው አዘዘው፡፡ ሣጅንም አንድ ጉራሽ ቀመሰና እንደገና ወደ ሣህኑ በመመለስ ከነፌስታሉ ሰጠኝ፡፡ እየሰጠኝ እያለ ‹‹ጓዴ ተረጋጊ ጉዳዩን እኛም ስለምንከታተለው እዚህ እሥር ቤት ልትቆይ የምትችለው የዛሬን ግፋ ቢል የነገን ነው፡፡›› በማለት ሊያረጋጋኝ ሞከረ፡፡ እኔም ‹‹እሽ›› አልሁና ተቀብዬ ገባሁ፡፡ እንደገባሁ ከአጠገቤ ሲያወራኝ የቆየውን እሥረኛ ‹‹እንብላ›› ስለው ‹‹አሁን በላሁ፡፡›› በማለት ሲግደረደር አጠንክሬ ስለምነው አብሮኝ መብላት ጀመረ፡፡ እየበላን እያለን በምን ምክንያት እንደታሠረ ጠየቅሁት፡፡ እሱም መኪና ሲያሽከረክር ሰው በመግጨቱ እንደሆነ ነገረኝ፡፡ ከዚያም በመጠኑ ስለተግባባን ብዙ ማህበራዊና ወቅታዊ ሁኔታዎችን እየተጨዋወትን አመሸን፡፡

**ይቀጥላል!!!**

# ‘የቤርጎ ቤቶቻችን’ ገመና

ጀማል ሙሀመድ ሀይሌ (ዶ/ር)
ከጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል
jemalmohammed99@gmail.com

“ሰውዬው ‘መናጢ ድሀ’ የሚባል አይነት ነው” አሉ፡፡ ድሀ ነውና እከክ ይይዘዋል፡፡ እናም ጓደኛውን ያማክረዋል፤ “የ’ከክ መድሀኒት ምንድነው?” በማለት፡፡

ጓደኛውም፣ “የ’ከክ መድሀኒትማ ቅቤና ማር መብላት፣ ስጋ መመገብ፣ መረቅ መጠጣት ነው” ይለዋል፡፡

እሱም፣ “የሀብታም-የሀብታሙማ መች ጠፍቶኝ፤ የድሀ-የድሀውን ንገረኝ አልኩህ’ንጂ” በማለት ይመልስለታል፡፡

“የድሀውማ፣ ምራቅህን እትፍ-እትፍ እያልክ ማከክ ነው” ብሎት እርፍ፡፡

ጀምበር የእለቱን ስራዋን ጨርሳ ጥልቅ እንዳለችና የእለቱ ጨለማም “መጣሁ፣ መጣሁ” ማለት ሲጀምር፣ የአሜሪካን ግቢ “አልጋ” (መኝታ ቦታ) አከራዮች፣ አውራ ጎዳናው ላይ ቁመው “መኝታ አለ!”፣ “የፍራሽ መኝታ አለ!”፣ “አልጋ አለ!” በማለት መወትወት ይጀምራሉ፡፡ አለባበሱ እንደ ነገሩ የሆነ፣ በእነሱ ግምት ድሀ ወይም የገጠር ሰው የመሰላቸውን ሲያዩ ድምፃቸውን በጣም ከፍ ያደርጉታል፡፡ አንዳንዶቹም የሚያከራዩበትን ዋጋ ጭምር ይናገራሉ - በጣም እርካሽ መሆኑን ለማመላከት፡፡

የአሜሪካን ግቢዎቹን የመሰሉ አከራዮች ባሕር ዳር ከተማም አሉ፡፡ ልዩነታቸው የስምሪት ሰአታቸውና “የማስታወቂያ” አሰራራቸው ነው፡፡ የባሕር ዳሮቹ ከምሽት ጋር ቀጠሮ የላቸውም፤ ስራቸውን የሚከውኑት ከቀን ጀምረው ነው፡፡ “መኝታ አለ!” እያሉም አይወተውቱም፤ በዚህ በኩል ጭምት ናቸው፡፡ በአውቶቡስ መናኻሪያው ዋና በር አካባቢ በመቆም፣ አንዳንዴም ከመንገዱ ዳር በኩል ቁጭ ብሎ በመጠበቅ ደንበኞቻቻቸውን ያጠምዳሉ፤ ማደሪያ ፈላጊ ምስኪን ወይም የገጠር ሰው የመሰላቸውን ወይም የገመቷቸውን ሰዎች ጠጋ በማለት ለስለስ ብለው ያናግራሉ፡፡

የአሜሪካን ግቢውም ሆነ፣ የባህር ዳሩ “መኝታ አለ” ጥሪዎች፣ በኢትዮጵያ የቤርጎ አገልግሎት የመጨረሻው ደረጃ ላይ የሚገኙት ናቸው፤ “የድሀ-የድሀውን ቤርጎ ንገረኝ” ላለሰው የሚጠቅሙ፡፡

ሌሎች ደግሞ አሉላችሁ፡፡ አንሶላቸው፣ ፎጣቸውና የትራስ ልብሳቸው ወተት የመሰለ ነጭ ወይም የቀለም አይነታቸው ምንም ይሁን ምን በንፅህና ያበዱ፤ የንፅህናን ጣሪያ የነኩ - ምናልባትም የራስን የቤት አልጋ ንፅህና ሊያስንቁ የሚችሉ፡፡ ታዲያ የነዚህ ቤርጎዎች ባለቤቶች “አልጋ አለ” የሚል ማስታወቂያ መለፈፍ ከፈለጉ፣ ወደ ጎዳና ሳይሆን “ኢቢሲ” በማለት በቅርቡ አዲስ ስም ወዳወጣው ቴሌቪዥን ጣቢያ ነው የሚሄዱት፡፡ እነዚህን መሰል አልጋዎች በኢትዮጵያ የቤርጎ አገልግሎት የመጀመሪያው ደረጃ ላይ የሚገኙት ናቸው፤ “የሀብታም-የሀብታሙን ቤርጎ ንገረኝ” ላለ ሰው የሚነገሩ፡፡

የእኔ ትኩረት ግን ከሁለቱም ላይ አይደለም፡፡ በሁለቱ መካከል ባሉት ቤርጎዎች ላይ ነው፡፡ ችግሩ ግን - በሀገራችን የሚከራዩ አልጋዎች ደረጃ የላቸውምና - በሁለቱ መሀል ባሉት የአልጋ ቤቶች መካከልም ሰፊ ልዩነት ያለ መሆኑ ነው፡፡ ዞሮ ዞሮ በጣም ዝቅተኛ ወደ ሆኑት ከሚጠጉት ወይም በጣም ዘመናዊ ወደ ሆኑት ከሚቀራረቡት አልጋ ቤቶች ጉዳይ የለኝም፡፡ ትኩረቴ “በጣም መካከለኛ” ሊባሉ ከሚችሉት ላይ ነው - መካከለኛ ገቢ ያለው ሰው በብዛት ከሚያድርባቸው የቤርጎ አልጋዎች ላይ፡፡ ስለሆነም ጨዋታችን “የመካከለኛ -የመካከለኛውን ቤርጎ ጉዳይ ንገረኝ” አይነት ነው፡፡

የቋንቋ ተመራማሪዎች ለአንድ ነገር ብዙ ስም ወይም የመጠሪያ አይነት መኖሩ፣ ነገሩ በህብረተሰቡ ውስጥ ያለውን ተፈላጊነት እንደሚያመላክት ይናገራሉ፡፡ የሚከራይ አልጋም፣ “ቤርጎ ቤት”፣ “አልቤርጎ”፣ “መኝታ ቤት”፣ “አልጋ ቤት” በሚሉ አራት ስሞች መጠራቱ የተፈላጊነቱ መገለጫ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ስለሆነም እንዳመቸኝ ሶስቱንም ስሞች እየቀያየርኩ እጠቀማለሁ - ጉዳዬ ከስማቸው ሳይሆን ከምግባራቸው፣ ከምግባራቸውም ደግሞ እንደ ግንባር ስጋ ፈጥጦ ከሚታየው ጉዳቸው ወይም ገመናቸው ላይ ነውና፡፡

የአንዳንዶቹ መኝታ ቤቶች ችግር ገና ከበሩ ሊጀምር ይችላል፤ በራቸው የሚዘጋውም፣ የሚከፈተውም በትግል ነው፡፡ አንዳንዴ ከተዘጉ በኋላ “ባባቴም የለ፤ አልከፈትም” የሚሉ የቤርጎ በሮች ያጋጥማሉ፡፡ አልጋ ተከራዩ ከውስጥ እያለ በተለይም ደግሞ በጧት ወደ መናኻሪያ ሊወጣ ሲል ከሆነ ለጊዜውም ቢሆን የሚፈጥረውን ድንጋጤ አስቡት፡፡ ያለው ምርጫ በሩን በመደብደብና በመጮህ የድረሱልኝ ድምፅ ማሰማት ብቻ ነው፡፡ “ይህ ሁሉ ለምን ይሆናል?” ከተባለ፣ መልሱ አጭር ነው፤ ባለአልጋ ቤቶች - ብዙዎቹ ማለት ይቻላል - በየእለቱ ለሚያከራዩዋቸውና ገቢ ለሚያስገኙላቸው የአልጋ ክፍሎች ተገቢውን ጥገና በወቅቱ ስለማያደርጉላቸው ነው፡፡ የብዙዎቹ ባለአልጋ ቤቶች ፍላጎት፣ የተጠቃሚው ምቾት ብቻ ሳይሆን ፍላጎትም ተጓድሎ ቢሆን እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ወጭ የማትነጥፈውን ላም ማለብ ብቻ ነው፡፡

> አልጋ የሚይዝ ሰው ... አልጋውን ሳያይ እንደማይዝ ይታወቃል፡፡ አልጋው ላይ በመቀመጥ ወይም ቢያንስ ቢያንስ እንደ ቆመ አልጋውን ጫን-ጫን በማለት ቢያንስ ሰባራ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ይሞክራል፡፡

አንድ መኝታ ቤት የውስጥ መፀዳጃ ክፍል ካለውና የመፀዳጃ ክፍሉ አምፑል ከተቃጠለ ብዙውን ጊዜ አይቀየርም፤ “ቀድሞውንም የተገጠመው በስህተት ነበር’ንዴ?” ያስብላል፡፡ ለዚህች አይነቷ ምስኪን ክፍል የሚሰራ አምፑል ሊቀየር የሚችልበት አጋጣሚ አንድ “ተጨቃጫቂ” ተጠቃሚ ከተከራያትና ምናልባትም “የሽንት ቤቱ አምፑል ይቀየርልኝ” ብሎ ድርቅ ካለ ብቻ ነው፡፡ አለበለዚያ እንደ ጨለመች ትከርማታለች ወይም አመታትን ታስቆጥራለች፡፡ ከዚህ የከፋው ግን የመፀዳጃ ቤቱ በር ችግር ያለበት ከሆነ ነው፡፡ የመፀዳጃ ቤቱ በር ለምሳሌ በሩ የማይዘጋ ከሆነ፣ የሚጠገንበትን ጊዜ መገመት አይቻልም፡፡ “ተጨቃጫቂ” ደንበኛ እንኳን የፈለገውን ያህል ቢሞግት ውጤት የማግኘት እድሉ በእጅጉ የጠበበ ነው፡፡ ስራው የበር ቁልፍ መግዛትን፣ ባለሙያ ማምጣትን፣ ከሁሉም በላይ ገንዘብ ማውጣትን ይጠይቃል፡፡ እንደ አምፑል በአስራ አምስት ወይም ሀያ ብር የሚገላገሉት ነገር አይደለም፡፡ እጅግ በጣም ብዙ የሆኑት መኝታ ቤቶች አንዱ ያልተፃፈ መርህ ደግሞ ትንሽ ገንዘብ እያወጡ ብዙ ማትረፍ ሳይሆን፣ በተቻለ መጠን ያለ ምንም ወጭ ማትረፍ፣ እያተረፉ ማትረፍ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አላስፈላጊ የሆኑትን ሳይሆን ከተቻለ ከአስፈላጊነትም አልፈው በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ወጭዎች ጭምር በመከላከል ማትረፍ ነው፡፡ እናም አንዴ የተበላሸ የመፀዳጃ ቤት የውስጥ በር ምናልባትም በአልጋ ቤቱ እድሜ ልክ ላይጠገንም ይችል ይሆናል፡፡

ከመኝታ ቤት የመፀዳጃ ክፍል በር ያለ መዘጋት ችግር ጋር የተያያዘ የቅርብ ጊዜ ገጠመኝ አለኝ፡፡ ቦታው ከስራ ባልደረቦቼ ጋር የተጓዝኩበት የወልደያ ከተማ ነው፡፡ መኝታ ቤቱ በቅርብ አመታት ከተገነቡ ህንፃዎች ውስጥ ከአንድ ሆቴል ፎቅ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ አልጋውን ካየሁ በኋላ በተጠየኩት መሰረት መታወቂያዬን በመስጠት ሂሳቡን ከፈልኩ፤ ባጭሩ ተከራየሁ፡፡ ከመፀዳጃ ክፍሉ ውስጥ የተገተረው ቧንቧ ውሀ ስለሌለው በባሊ የቀረበውን ውሀ እየጠለኩ ሻወር በመውሰድ የመንገደኛ ላቤን ካስወገድኩና ድካሜን ከቀነስኩ በኋላ እራት ለመብላት ወጣሁ፡፡ ወልድያን ውስጣውስጧን በሚያውቅ ባልደረባችን መሪነት ከሄድንበት ምግብ ቤት “ነገም ከነገ ወዲያም በደገምኩት” የሚያስብል እራት በላን - አትክልት በዳቦ፡፡

እንደ ተመለስኩ የመኝታ ቤቴን ክፍል ገና ስከፍት፣ “እንኳን ደህና መጣህ” አለኝ - እጅግ አስቀያሚ የሆነ ሽታ፡፡ ቶሎ ብዬ ወደ መስኮቱ አመራሁ - ትኩስ አየር ወደ ውስጥ በማስገባት መጥፎውን ሽታ ለማባረር፡፡ መስኮቱ ግን እንደ ተከፈተ ነበር፡፡ ሽታው ከመፀዳጃ ክፍሉ እንደሚመጣ ስለተረዳሁ አሁንም ፈጠን ብዬ ወደ መፀዳጃ ክፍሉ በመግባት ከባሊው ላይ የቀረውን ዉሀ ከመፀዳጃ ቤቱ መቀመጫ ላይ ደግሜ-ደጋግሜ ደፋሁ፡፡ ከንጋት በፊት ላለው ሶላቴ (ስግደቴ) ጭምር ውሀ ስለሚያስፈልገኝ ወጣቱን አልጋ አከራይ በተጨማሪ ውሀ እንዲሰጠኝ ጠየኩት፡፡ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሀያ ሊትር የሚይዘውን ጀሪካን አመጣልኝ ጀሪካኑ ሙሉ ነው፡፡ የወጣቱ ቸርነት እየገረመኝ ውሀውን ሞቅ ካለ ምስጋና ጋር ተቀበልኩ፡፡

አሁንም በጣም በዛ ያለ ውሀ ከመፀዳጃ ቤቱ መቀመጫ ላይ ከደፋሁ በኋላ፣ የመኝታ ቤቱን መስኮት ዘግቼ ሻይ ልጠጣ ወጣሁ፡፡ ስመለስ ያ መጥፎ ጠረን እንደ ገና ክፍሉን ተቆጣጥሮታል፡፡ ምንም ያህል ለውጥ እንደማያመጣና ከፍቼ ማደር እንደማልችል ቢገባኝም ለጊዜው ፋታ ለማግኘት ያህል መስኮቱን ከፈትኩት፡፡ ከዚያም አንድ የመጨረሻ አማራጭ ለመሞከር ወሰንኩ - የመፀዳጃ ቤቱን በር መዝጋት፡፡ ሆኖም ምኞቴ ሜዳ ላይ ቀረ፡፡ በሩ አንደኛ እጀታ የለውም፡፡ እጀታ ተገጥሞበት የነበረው ሁለት ወይም ሶስት ቀዳዳዎች ብቻ ናቸው ከበሩ ላይ ያሉት፡፡ ሰፋ ባለው ቀዳዳ ጠቋሚ ጣቴን በማስገባት ለመዝካት ሞከርኩ፤ “አልዘጋም” አለ፡፡ በሀይል መታ በማድረግ ለመዝጋት ሞከርኩ፤ “አልዘጋም” አለ፡፡ እንደ ገና በጣም በሀይል በመምታት ለመዝጋት ሞከርኩ፤ “አልዘጋም” አለ፡፡ የመፀዳጃ ወረቀት በበሩ ጠርዝና በመቃኑ መካከል በማጉረስ ለመዝጋት ሞከርኩ፤ “አልዘጋም” አለ፡፡ የወረቀቱን መጠን በመጨመር፣ ጥቅሉን ደጉስ አድርጌ እንደ ገና ሞከርኩ፤ “እዘጋለሁ” አለ፤ ማለትም ተዘጋ፡፡

ሆኖም መቶ ብር ለከፈልኩበት የአከራዮቼ አልጋ ቤት የውስጥ በር

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# የማሕበረሰብ አገልግሎት የልምድ ልውውጥ ጉዞ

በታድየ አስማረ

የአንድ ሀገር የእድገት ደረጃ የሚለካው የሕዝቧ የኑሮ ደረጃ ሲሻሻል መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ የሕዝቡ የኑሮ ደረጃ ተሻሻለ ሲባል ደግሞ ከግለሰብ ጀምሮ እስከ ማሕበረሰብና ህብረተሰብ ድረስ ይደርሳል፡፡ የሀገራችን ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይህንን እውነታ ተግባራዊ በማድረግ በአካባቢያቸው የሚገኙትን ነዋሪዎች የኑሮ ደረጃ እንዲሻሻል ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም በምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ጽ/ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት አማካኝነት የማሕበረሰብ አገልግሎት በመስጠት አገልግሎቱን እየሰጠ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ውጤታማ እየሆነ ይገኛል፡፡ ተጠቃሚ የሆኑ የማሕበረሰብ ክፍሎችም የተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በቅርቡ በዩኒቨርሲቲው የማሕበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር የሚመራ ከ30 በላይ አባላትን የያዘ ቡድን በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ላይ የስራ ጉብኝት አካሂዷል፡፡ ቡድኑ ከየፋካልቲ፣ ኮሌጅ፣ ኢንስቲትዩት፣ አካዳሚና ት/ቤት የተውጣጡ የማሕበረሰብ አገልግሎት አስተባባሪዎችና ፈፃሚ ባለሙያዎችን ያካተተ ሲሆን ወደ ደብረታቦር፣ ወልዲያ፣ መቀሌ፣ አክሱምና ጐንደር ዩኒቨርሲቲዎች በመጓዝ የልምድ ልውውጥ አካሂዷል፡፡

የጉብኝቱ ዋና ዓላማ የዩኒቨርሲቲው የማሕበረሰብ አገልግሎት ስኬታማ እንዲሆን ከሌሎች አጋር አካላት ልምድ በመውሰድ ለቀጣይ ጠንካራ ጎኖችን ይበልጥ በማጠናከር ክፍተቶችን በመሙላት የተሻለ ስራ ለመስራት ነው፡፡ በልምድ ልውውጡ የስራ ክፍሉ አወቃቀር፣ የባለሙያ አመዳደብና አመራረጥ፣ የስራው አተገባበር፣ ተግዳሮቶች፣ ስኬቶች፣ የበጀት አመዳደብና ስርጭት፣ የአመራሩ ሁኔታ እና የመሳሰሉ ጉዳዮችን አካቷል፡፡ በተጨማሪ በ2006 ዓ.ም የማሕበረሰብ አገልግሎትን የሙያቸውና የአገልግሎታቸውን ክፍያ ሳይጠይቅ ማሕበረሰቡን የሚጠቅሙ ስራዎችን ለሰሩ የዩኒቨርሲቲው ምሁራንን ለማበረታታት የተለያዩ ጥንታዊና ታሪካዊ ቅርሶቻችን ማስጎብኘት አላማ ያደረገ ጉዞ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የተለያዩ ጥንታዊ ቅርሶች የሚገኙባት ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሰራሽ የሆኑ የስነ ህንፃና የስነ ጥበብ እንዲሁም ጥንታዊ የስነፅሁፍ መገኛ መሆኗ ይታወቃል፡፡ እነዚህን ቅርሶች ጐብኝቶ መመለስ የቡድኑን ጉብኝት የተሟላ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ጉዞ ቡድኑ ከደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ በመነሳት ጐንደር ዩኒቨርሲቲን የጉብኝቱ ማስረጊያው በማድረግ ወደ ባሕር ዳር ተመልሷል፡፡

## ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ

ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ ከመድረሱ በፊት የቡድኑ የመጀመሪያ ጉብኝት የአውራምባ ማሕበረሰብ ነው፡፡ የማሕበረሰቡን አኗኗርና የስራ ባሕላቸውን፣ ማህበረሰቡ ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ አሁን ያለበት የኑሮ ደረጃ እንዲሁም የስራ ድርሻ ላይ የፆታ ክፍፍል የሌለበት መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

ደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ የደረስነው የምሳ ሰዓት አካባቢ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲውን የአስተዳደር አካላት ማግኘት ባንችልም የተለያዩ ክፍሎችን መጐብኘት እንደተቻለ በተለይ ቤተ መፃሕፍቶች ለአካል ጉዳተኞች የማንበቢያ ክፍል አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማሟላት የእኩል ተጠቃሚነት ለማድረግ የተሰራው ስራ የሚበረታታ ነው፡፡

ከደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ በመቀጠል በቀደምት አባቶቻችን እጅ የታነፀውን ውብና ማራኪ የጥበብ አሻራ ያለበትን የጨጨሆ መድኃኒያለም ቤተ ክርስቲያን ጎብኝተናል፡፡ በመቀጠል ከጋሸና ከተማ ወደ ግራ በመታጠፍ ወደ ጥንታዊቷ ላሊበላ ከተማ ጉዞ ተደረገ፡፡ የላሊበላ ከተማ የተመሰረተችው በ12ኛው ክፍለ ዘመን በዛግዌ ስርዎ መንግስት በንጉስ ላሊበላ ነው፡፡ ንጉስ ላሊበላ ደግሞ ለ40 ዓመት ያህል ያስተዳደረ ሲሆን በንግስናው ዘመን ለ23 ዓመታት ከአንድ ወጥ ድንጋይ የተፈለፈሉ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን ሰርቷል፡፡ የላሊበላን ውቅር አብያተ ክርስቲያን ለማስጐብኘት የተመደቡልን መነኩሴ የላሊበላን ቅድስና፣ ንግስና፣ የህንፃ ጥበብ እና የከተማዋ አመሰራረትን በዝርዝር ተርከውልናል፡፡ ቅዱስ ላሊበላ ከ13 ዓመት የእስራኤል ጉብኝት መልስ በመንገስ በዘመኑ የማይታሰቡ የስነ ህንፃ ጥበብ አበርክቷል፡፡ እነዚህ የስነ ጥበብ ስራዎች በርካታ ቱሪስቶችን በመሳብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡







የልዑካን ቡድኑ በጉብኝት ወቅት

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# በአድዋ ድል - ማንነት፣ አንድነት፣ ነጻነት…

በብርሃኔ አለሙ (ሶሻል አንትሮፖሎጂ ዲፓርትምንት)

“የቅኝ ግዛት ዳር ዳርታው ለቅኝ የታጩ ህዝቦችን የሰውነት መታወቂያ መንጠቅ ነው” እንዲል በእውቀቱ ስዩም አውሮፓውያን መንግስታት ቅኝ ግዛትን የጀመሩት የጥቁሮችን ማንነት ጥላሸት በመቀባት ነበር፡፡ እናም አንዴ ከስልጣኔ ጎራ እያራቁ በድንቁርና እየፈረጁ ሌላ ጊዜ ከሰው ተራ እያወጡ ከእንስሳ እያዛመዱ ሲቀጥልም አፍሪካዊያን ‘በእጭነት’ ደረጃ የሚገኙ ዘሮች ናቸው እያሉ በዘረኝነት ቅባት የታጀለ መርዝ በመርጨት ነበር መታወቂያ ንጥቂያውን ‘ያሳለጡት’፡፡ ይህን አይነት የተዛባ አመለካከት እና እሳቤ ከማስራጨታቸው በተጨማሪ አፍሪካዊያን ከአውሮፓውያን የስልጣኔ ቱርፋት ተካፋይ ይሆኑ ዘንድ በኛ ስርዓት መተዳደር ወይም ማደር ግድ ነው የሚል ጠማማ አቋም በመያዝ ነበር በቢስማርክ ደጋሽነት ወደተዘጋጀው ቅርጫ ያመሩት፡፡

በርሊን ላይ በጠረጴዛ ዙሪያ ከበው ብጣሽ ካርታቸው ላይ ብዕራቸውን ወደሩ ፡፡ በእምቅ ሃብቷ አምሮት ለሃጫቸው ዘብ እያለ አፍሪካን በብዕር ካራ እንደ ሰንጋ አርደው በለቷት፡፡ በዚህ ጊዜ በአንድ ነገር እርግጠኛ ነበሩ፤ እድል ካልጠመመባቸው ጥቁር ነጭን በጦር እንደማያሸንፍ፡፡ ከተገኙዎች ጦር በላይ የሚያሳስባቸው በገዥዎች መካከል ሊፈጠር የሚችል የፍላጎት መጣረስና ከስምምነት ማፈንገጥ ነበር፡፡ እናም ወረቀት ላይ በረቂቅ ያስጎመዥቸው በውን ይፈጸም ዘንድ መተባበር የሚል ሕቡ መርህ አስቀመጡ፡፡ ከቂራ መልስ ቀጥታ በአራቱም አቅጣጫ ወደ አፍሪካ ይጣደፉ ጀመር፤ የአፍሪካን የድንግልና ሪባን ለመበጣጠስ፡፡ በተወሰኑ አመታት ውስጥም አፍሪካዊያንን በጦርም በአሻጥርም ወረሩ፡፡ (የአፍሪካዊያን ታሪካቸው ተደለዘ’ ሃብታቸው ተጋዘ’ ጥቁርነታቸውም ተወገዘ’’ ለዘመናት በኩራትና ነጻነት የኖሩባት አህጉር የነጭ መፈንጫ ሆነች፡፡)

እንግዲህ በዚህ ጊዜ ጣልያንም የክፍተቷ መሙያ የማነነቷ ማሳያ የፍላጎቷ ማርኪያና የችግሯ ማራገፊያ ትሆን ዘንድ በማሰብ እድሜ ጠገቧን እማማ ኢትዮጵያን አጨች፤ ያለ እድሜ ጋብቻ ይሏል ይህ ነው፡፡ እንደ ግብረ አበሮቿ በንግድም በሰነድም ማጭበርበሩን ተያያዘችው፡፡ በዚህ መንገድ የተወሰኑ ቦታዎች ላይ መስፈር ቻለች፡፡ እያደር ግን ኢትዮጵያን የመጠቅለል እቅዷ ይፋ ወጣ፡፡ በተለይ “የውጫሌ ውል” እየተባለ በታሪክ የሚጠራው ሰነድ ከጀርባ ያዘለው መርዝ ይፋ ሲወጣና ወይም በኢትዮጵ በኩል ሲሰረዝ የአሻጥር ስልቷ መክሸፉን አረጋገጠች፡፡ የውሉ መሰረዝ ወይም ኢትዮጵያ የጣልያን ጥገኛ አይደለሁም አልነበርሁምም የሚል የነጻነት መግለጫዋን የሰሙ አውሮፓውያን ጣልያን ኢትዮጵያ ለመጉረስ አጋጣሚ ተፈጠረላት ይሉ ጀምረዋል፡፡ ባራቴሪም “…በቅርብ ቀን ምኒልክን ብቀፎ ውስጥ አስሬ ሮማ አመጣዋለሁ…” (ጳውሎስ ኞኞ 2006’ 163) ብሎ በመናገር ታብዮ ነበር፤ አይ! ግብዝነት ደጉ¡

ጣልያን ድንበር ላይ ተጎልታ ስታልም የነበረው ሙሉ ኢትዩጵያን የመውረር ሴራዋ አደባባይ የዋለው እና በሰፊው ወደ ውስጥ መግፋት የጀመረችው የውጫሌ ውል እርባና ቢስ እንደሆነ ካረጋገጠች በኋላ ይመስላል፡፡ የራስ አሉላን ክንድ ዶጋሊ ላይ ያልቀመሰች ይመስል ‘ተይ ባለሽበት እርጊ’ ብትባልም ጆሮ ዳባ ልበስ ብላ ጉዞዋን ቀጠለች፡፡ በዚህ ጊዜ የልብ ልብ የሰጣት ኢትዮጵያውያን በውስጣዊ ችግሮቻቸው ምክንያት የጎሪጥ እየተያዩ ስለሆነ ጣልያን ላይ በአንድነት ሊዘምቱ አይችሉም የሚል ያልተጨበጠ ወሬ ነበር፡፡ በርግጥ “ሁለት ውሾች በአንድ አጥንት ሊጣሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አንድ ጅብ ቅርምቱን ሊቀላቀል ቢሞክር ሁለቱ ውሾች ይተባበሩበታል” በማለት ኢልግ እውነታውን ነግሯቸው ነበር፡፡ ከምኒልክ ወዳጅና አማካሪ ኤልግ ከነገራቸው እውነት ይልቅ ባራቴሪ ‘..ራሶች ሁሉ ተለያይተዋል፡፡ ሁሉም የሚሰራውና የሚያስበው የየግሉን ጉዳይ ብቻ ነው…” (ጳውሎስ ኞኞ 2006’ 164) በማለት የተናገረውን ከንቱ ምኞት የፈጠረው ወሬ በመውሰድ ወደ ትግራይ እየተንፋቀቀች ብዙ ቦታዎችን ለመቆጣጠር ሞከረች፡፡ የምኒልክን ዝምታና መዘግየት እንደፍርሃት በመቁጠር አክሱምን ወረረች፤ “አይጥ ለሞቱ የድመት አፍንጫ ይልሳል” እንዲሉ፡፡ “በኢትዮጵያ ታሪክ ያለፉ ነገስታት በሙሉ የማይደራደሩበት ነገር ቢኖር አክሱምን ለጠላት አሳልፎ መስጠት ነው፡፡ የምኒልክ ዝምታ መሰበር የተጀመረው ከአክሱም መያዝ በኋላ ነበር” (ሙሉቀን ታሪኩ 2006’124)

ምኒሊክ ይህን ጊዜ

> “…እንግዲህ ብሞትም ሞት የሁሉ ነውና ለእኔ ሞት አላዝንም፡፡ …አሁንም አገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት እግዚአብሄር የወሰነልንን የባህር በር አልፎ መጠቷልና እኔም የአገሬን ከብት ማለቅ የሰውን መድከም አይቼ ዝም ብልው ደግሞ እያለፈ እንደ ፍልፍል መሬት ይቆፍር ጀመር፡፡ አሁን ግን በእግዚአብሄር እረዳትነት አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም፡፡ ያገሬ ሰው…ጉልበት ያለህ በጉልበትህ እርዳኝ፡፡ ጉልበት የሌለህ ለልጅህ ለሚስትህ ለሃይማኖትህ ስትል በሃዘን እርዳኝ፡፡ ወስልተህ የቀረህ ግን ኋላ ትጣላኛለህ፡፡ አልተውህም፡፡ ማርያምን ለዚህ አማላጅ የለኝም፡፡”

በማለት የደም ግብር ለነጻነት ይከፍል ዘንድ የክብር ጥሪያቸውን አስተላለፉ፡፡ የምኒልክ ነጋሪት ተጎሰመ፤ ክተት ሰራዊት እያለ የእናት አገር ጥሪ መልዕክቱን አስተጋባ፡፡ ካለነጻነት ከመኖር በክብር መሞትን የሚመርጡት ኢትዮጵያውያን ብሄር ሳይቆጥሩ’ ሃይማኖት ሳይለዩ’ ፆታና እድሜ ሳይመርጡ- ‘እረ ጉዱ እረ ጉዱ በዛ፤ በጀልባ ተሻግሮ [ኢትዮጵያን] ሊገዛ ’ -በማለት እየሸለሉ ወደ ሰሜን በአንድነት ተመሙ፡፡ “ለንጉሰ ነገስቱ ነጻነትና የአገር ድንበርን ለማስከበር ጥሪ ጦር ያልላከ የአገሪቱ ክፍል አልነበረም”ይላሉ ባህሩ ዘውዴ (2003’ 85) ዘማቹ ከመላ ኢትዮጵያ የተውጣጣ መሆኑን ሲገልጹ፡፡ ፓውሌቲ የተባለ ጣሊያናዊም “…ህዝቡ ከሁሉም ብሔረሰብ ተውጣጥቶ ቀርቧል…” በማለት ስለብሔር ስብጥሩ፤ “…ህዝቡ በሙሉ ተነቅሎ ለወረራ የሚሄድ ይመስላል…” ሲል ደግሞ ስለብዛቱ ጳውሎስ ኞኞ (2006)፡፡ መስክሯልጳውሎስ ሚሊኪያስ (ዶ/ር) እንዲህ ይላሉ፤ *“It knew no class, no boundaries, no religious denomination, no age group…”* በአጭሩ “የምኒልክ ጦር በቁጥር ብዛት ብቻ ሳይሆን ድፍን ኢትዮጵያን የወከለ በመሆኑ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ነበር” ባህሩ ዘውዴ (2003)፡፡

በመሆኑም የአድዋ ጦርነት የኢትየጵያዊያን የአንድነት ምስጢር ሳጥን (black box) ነው ብንል ስህተት አይሆንም፡፡ ይህ ሲባል ግን አንድነታችን የተመሰረተው በጦርነቱ ወቅት ነው ማለት አይደለም፡፡ አንድነት እንደ ድሃ ጎጆ በአንድ ጀንበር የሚገነባ አይደለም፤ በዘመናት ውጣ ውረድ እንጂ፡፡ አዎ! “…በሰላም ጊዜ ተባባሪ በዘመቻ ጊዜ ጀብደኛ በጦርነት ጊዜ መንፈስ ቆራጥ የሚያደርግ የወንድነት ሃሞትን የሚያፈላ ያርበኝነት ወኔን የሚያገነፍል የድፍረት ግመት የማያሞኘው አንድነት ነው…” (“አደፍስ” 2006’82 በዳኛቸው ወርቁ)፡፡ ከጦርነቱ በፊት የህዝቦች ትስስር እንደነበር የፍስሃ ያዜን ዐ.ነገር ልጥቀስ፤ “በምኒልክ ንጉሰ ነገስትነት ዘመን በተለይ በአድዋ ጦርነት ዋዜማ ኢትየጵያዊያኑ ሙሉ ለሙሉ አንድነታቸውን ያረጋገጡበት ወቅት ነበር”(“የኢትዮጵያ የ5ሺ ዓመት ታሪክ፤ ከኖኅ እስከ ኢህአዴግ” 2003’ 435)፡፡ በአጭሩ የአድዋ ጦርነት ከውጣ ውረዶች አንዱ፤ ነጻነታችንን ያረጋገጥንበት እና እድሜ ጠገብ አንድነታችንን በአደባባይ ያሳየንበት እንዲሁም ያረጋገጥንበት ልዩ ክስተት ነው፡፡ “ነጻነትና አንድነት መንዮች ናቸው”

አሁን ላይ ሆነን ስናስበው አስገራሚ የሚሆንብን ሌላው ጉዳይ “ከአዋጁ በፊት ኢትዮጵያ ብሄራዊ ጦር ሰራዊት አልነበራትም፡፡ ቢሆንም … በሀገሩና በሃይማኖቱ ስም ለሚደረግለት ጥሪ ህዝቡ በፍጥነት ምላሽ በመስጠት ይታወቃል” (ሙሉቀን 2006)፡፡ ይህን ጠንቅቀው ስለሚያውቁም ነው እትጌ ጣይቱ ለአንቶኔሊ “ እግሩን ለጠጠር ደረቱን ለጦር ሰጥቶ አገሩን የማያድን ሰው የሌለ አይምሰልህ በገዛ ደሙን ገብሮ ለገዛ አገሩ መሞት ጌጡ ነው ሞት አይባልም…” በማለት ቁርጡን ያሳወቁት፡፡ ይህ የእተጌ ጣይቱ መግለጫ ነጻነትን በመግደል ሳይሆን በመሞት መቀዳጀት የሚል የጦርነት ፍልስፍና ይመስላል፡፡ እጅጋየሁ ሽባባውም (ጂጂ)

> “በደግነት በፍቅር በክብር ተጠርቶ’
> በክብር ይሄዳል ሰው ሊኖር ሰው ሞቶ”

ስትል የብልኋን ንግስት ፍልስፍናና የእምዬ ምኒልክን ጥሪ ክቡርነት ታጸናለች፡፡ በቃ! የአድዋ ዘመቻ እኮ ሰው ሞቶ ሰው ለማኖር የተደረገ ነው፡፡ ፈጣሪን መንገድ በመከተል የተደረገ ዘመቻ፤ በሞቱ ለሰው ልጅ ህይወት እንደሰጠው አይነት፡፡ አዎ! የአድዋ ድል የሰው ህይወትን በመክፈል የነጻነት ዋጋዋ ስንት እንደሆነ ጠንቅቀን የምናውቅ መሆናችንን ያስመሰከርንበት ድል ነው፡፡

-----------//------------

ጣልያን በሰላም እንድትለቅ በተደጋጋሚ ብትጠየቅም በጀ ባለማለቷ የጦርነቱ ፊሽካ የተነፋው አምባላጌ ላይ ነበር፡፡ “ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው” ነውና በነራስ መኮንን እና ፊትአውራሪ የሚመራው ሰራዊት በጣላያን ላይ መዐቱን ያወርደው ጀመር፡፡ የጣልያን ጦር በሁለት ሰዓት ውስጥ ብትንትኑ ውጥቶ እግሬ አውጭኝ እያለ ፈረጠጠ፡፡ “ድራማዊ” ይሉታል ፕሮፌሰር ባህሩ ይህን የአምባላጌውን ውጊያ፡፡ በቅርብ ርቀት ሆነው የጣልያንን መሸነፍ የሰሙ የምኒልክ ወታደሮች ጦርነቱ የተጠናቀቀ ስለመሰላቸው በማዘን “ይህን ሁሉ መንገድ ተጉዘን የመጣነው ሳንዋጋ ለመመለስ ነበር?” ሲሉ ነበር፡፡ ዶ/ር ፓውሎስ ሚልኪያስ ስለወታደሩ ቁጭትና ሃዘን እንዲህ ይላሉ “… *after being informed that the battle of Amba Alaghe was concluded in Ethiopia’s favor, those galloping towards the site dismounted their horses with anger and grief and those walking on foot sat down and cried because they had been denied the opportunity to participate in the action”.*

እንዴት አይዘኑ ለነጻነት የሚደረግ ትግል ላይ አሻራን አለማሳረፍን የመሰለ ምን አሳዛኝ ብርቱ ጉዳይ ይኖራል!

-----------//----------

ከአምባላጌ የሸሸው የጣልያን ጦር ሃይሉን አጠናክሮ መቀሌ ላይ መሸገ፡፡ “ግድየላችሁም ጦርነት ለእናንተም ለእኛም አይበጅም በሰላም ልቀቁ” ቢባሉም የታጠቁትን ዘመናዊ የጦር መሳሪያ እየጠቀሱ መዘባበት ቀጠሉ፡፡ ኢትዩጵያዊያንም ከአምባላጌ ድል የባሩድ

ወደ ገጽ 15 ዞሯል

# ‘የቤርጎ ቤቶቻችን’ ...

*ከገጽ 7 የዞረ*

ያደረኩት ጊዜያዊ “ጥገና” ብዙም ውጤት እንደሌለው ወዲያው ገባኝ። በሩ ከመቃኑ ጋር መቶ በመቶ ልክክ አላለምና እየሸሸሁት ካለው መጥፎ ሽታ አዳሬን ማምለጥ አልችልም፤ ነገማ የታባቱ ያገኘኛል። ከዚህ የሚጠነባ ክፍል ውስጥ ማደር እንደሌለብኝ ወሰንኩ። እናም ፈጠን ብዬ ከፎቁ በመውረድ ለአከራዬ ክፍሉ ያለበትን ችግር አስረዳሁ። መጀመሪያ ላይ ሌላ ክፍል ለመስጠት ጥሩ አዝማሚያ ካሳየኝ በኋላ፣ “አንተ የተውከውን ክፍል የሚከራይልኝ የለም” በማለት ሊሰጠኝ ፈቃደኛ አልሆን አለ። እንደ ገና ላግባባው ሞከርኩ፤ “ወይ ፍንክች” አለ።

ስለሆነም እኔም አቀራረቤን ቀየርኩ፤ “ነገ እዚህ ከተማ ስለምቆይ ለጤና ጥበቃ እከሳችኋለሁ” አልኩት። ወጣቱ ትንሽ ዝም ብሎ ቆየ፤ እኔም ዝም ብዬ ጠበኩት። ያልጠበቀው የመብት ጥያቄ ለቀረበለት የዚህ አይነቱ ሰው የሚያስብበት ትንሽ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ከዚያም ተነስቶ ሄደ፤ ትንሽ ቆይቶ “አለቅዬው” መጣ። እንደዚያ ከሚገማ ክፍል ውስጥ ሳድር እንደማልችል ብቻ ነገርኩት - ቀሪውን ነገር አከራዩ እንደ ነገረው በመገመት። የአልጋ ክፍል ቁልፎች ወደሚንጠለጠሉበት ቦታ በአገጩ ምልክት በማሳየት ብቻ ለወጣቱ “መመሪያ” ሰጠው። እፎይ - ክፍል ተቀየረልኝ። ሲለምኑትና ሲያግባቡት “እምቢ” ያለን አንዳንዴ ማስፈራራት ሳያዋጣ አይቀርም። አሁን ሳስበው ግን ከማስፈራራቱ ይልቅ ከመታወቂያዬ ላይ ያለችው ዶ/ር (ዶክተር) የምትል ፅሁፍ ዋናውን ሚና የተጫወተች ይመስለኛል።

አልጋ የሚይዝ ሰው፣ አልጋውን ሳያይ እንደማይዝ ይታወቃል። አልጋው ላይ በመቀመጥ ወይም ቢያንስ ቢያንስ እንደ ቆመ አልጋውን ጫን-ጫን በማለት ቢያንስ ሰባራ አለመሆኑን ለማረጋገጥ ይሞክራል። ከዚህ እልፍ ያለው መስኮቱ መዘጋት አለመዘጋቱን፤ የአልጋ ቤቱ በር መቆለፍ አለመቆለፉን ያረጋግጣል። ሁሉንም ነገር ማረጋገጥ ግን እንዴት ይቻላል? ለምሳሌ በተገላበጡበት ቁጥር ሎሉታውን የሚያስነካ አልጋ ያጋጥማል። የዚህ አይነቱን አልጋ “ጤንነት” እንዴት አድረጎ በማየት (“ቼክ” በማድረግ) አልጋውን መረከብ ይቻላል? አከራዩ እያሳየ ወይም እያሳየች እንዳለች ከላዩ ላይ ጋደም ብሎ በመገላበጥ ወይስ በመንከባለል? በተለይ በዝናብ ወቅት የሚያፈስ ጣሪያ ያለውን መኝታ ቤት እንዴት አይቶ መረከብ ይቻላል? ጣሪያ ላይ በባሊ ውሀ ይዞ አይደፋ ነገር? ይህን የሚያደርጉት የሚያፈስ ጣሪያ ወይም አሸንዳ (ጎረንዳዮ) የጠገኑ ባለሙያዎች ናቸው። እርግጥ ነው የቤት ቆርቆሮ ጥንካሬን ለማሳየት፣ ጣሪያ ላይ ወጥተው ቡና የሚወቅጡም አይጠፉም። እነዚህ በ“ኢቲቪ” (ኢቢሲ) ማስታወቂያን በፌዝ የሚያቀርቡ ናቸው። አልጋ ተከራይ ደግሞ ፌዝ ላይ አይደለም ያለው።

ይህ ማለት ግን አልጋ ሲከራዩ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ አያስፈልግም ማለት አይደለም። በጣም በጣም አስፈላጊ ነው። የሚከራዩትን አልጋ አይቶ ከመረከብ አንፃር አንዱ ዋና ችግር የአንሶላ ጉዳይ ነው። ብዙዎቹ አልጋ ቤቶች ወይም አልጋ አንጣፊዎቻቸው ያገለገለን አንሶላ ሳያጥቡ ደግመው ያነጥፋሉ። በተለይ ሁለት ጊዜ ማንጠፍ በአብዛኞቹ አልጋ ቤቶች በጣም የተለመደ ነው። አንሶላውን ወይ ማጠብ ወይም በሌላ በታጠበ አንሶላ መቀየር ሲገባቸው፣ አንዱ ዛሬ በተኛበት አንሶላ፣ ነገ ሌላው እንዲተኛበት ያደርጋሉ። አንድ ጊዜ ታጥቦ የተነጠፈን አንሶላ ሁለት ሶስት ጊዜ ወይም ከዚህም አልፈው አንሶላው ያለበት ቆሻሻ ጎልቶ እስከሚታይ ድረስ ሳያጥቡ ደጋግመው ያነጥፉታል።

ሌላ ሰው ሲገላበጥበት ካደረ አንሶላ ላይ፣ የሌላን ሰው ገላ ሲሞስሙስ ካደረ አንሶላ ላይ ማደር ያልፈለገ የአልጋ ተከራይ ምን ያድርግ? ለዚህ ችግር በጣም ውጤታማው መንገድ ከቀድሞ የጋዜጠኝነት ባልደረቦቼ የተማርኳት ዘዴ ናት። አቶ ተከራይ አልጋውን ከመከራየቱ በፊት በቂ ብርሀን እንዲያገኝ የክፍሉን መብራት ያብራው ወይም መስኮቱን ይክፈት፤ ከዚያም አልጋው ላይ ከመቀመጡ ወይም እቃ አልጋው ላይ ከማስቀመጡ በፊት፣ የተነጠፈውን አልጋ - የላይኛውን አንሶላ በመጨመር - እስከ መካከል ድረስ በደንብ ይግለጠው። ከዚያም በታችኛው አንሶላ ላይ፣ በመካከል አካባቢ ወገብ-ለወገብ አግድም ያለፈ ቀጭን መስመር ይፈልግ - አንሶላው ታጥቦ ሲሰጣ የሚቀረውን የተሰጣበትን ሽቦ ወይም ገመድ ፋና። ለአዳር ቀርቶ ለተወሰኑ ደቂቃዎች አልጋው ከተተኛበት አንሶላው የተሰጣበት ሽቦ ወይም ገመድ ፋና ሊገኝ አይችልም። ፋናው ካልተገኘ ግልፅ ነው፣ አልጋው ላይ የተነጠፈው አንሶላ ከታጠበ በኋላ ቢያንስ ለአንድ ሰው አገልግሎት ሰጥቷል።

ሁለተኛው በልምድ ያገኘሁት ዘዴ የታኛውን አንሶላ የመጨረማመት ሁኔታ ወይም ደረጃ መለካት ነው። አንድን አንሶላ ለማጠብ ሲባል በሚካሄደው ፍግፈጋና ማሸት ምክንያት ከአንሶላው ላይ “ታትሞ” የሚቀረው ጭርምትና ሰው ስለተኛበት “ታትሞ” የሚቀረው ጭርምት ለየቅል ናቸው፤ ልብ ብሎ ላየው ሰው ሁለቱ ጭርምቶች በአንሶላው ላይ የሚተውት ቅርፅ በጣም ይለያያል። አልጋው ላይ ሰው በመተኛቱ ምክንያት የሚፈጠሩት ጭርምቶች ረዘም-ረዘም ብለው፣ ጎላ-ገላ ያሉና ወጥነት ያላቸው መስመሮች ሲሆኑ መገኛ ቦታቸውም ባብዛኛው ትከሻና የላይኛው የወገብ ክፍል በሚያርፍበት አካባቢ ላይ የተሰወነ ነው። በትጥበት ምክንያት የሚከሰቱት ጭርምቶች ጎልተው የማይታዩ፣ ወጥነት የሌላቸውና ደካማ ከመሆናቸውም በተጨማሪ አንሶላው ላይ የትኛውም ቦታ ላይ ሊገኙ የሚችሉ፣ አንሶላው ትንሽ ወጠር ተደርጎ በመነጠፉ ምክንያት ብቻ እጅግ በጣም ሊደበዝዙ ወይም ከናካቴው ሊጠፉ የሚችሉ ናቸው።

ከላይ የተጠቆሙት ሁለቱ ዘዴዎች የአንሶላ ንፅህናን ለማረጋገጥ በጣም ጠቃሚ ቢሆኑም፣ አንሶላው አዲስ ታጥቦ የተቀየረ መሆኑን ከማረጋገጥ የዘለለ አቅም ግን የላቸውም። በመሆኑም አልጋ ተከራዩን ሌላ ችግር አያጋጥመውም ማለት አይደለም። ለምሳሌ የአንሶላዎቹን ንፅህና አረጋግጦ የተኛ የአልጋ ተከራይ፣ እንደ ሳማ የሚያንገበግብ የተራቡ ቁንጫዎችን ቁንጥጫ ሲቀምስ ሊያድር ይችላል። ትኋን በአለብላቢት ምላሱ ሲልሰው የሚያድርበት አጋጣሚም ይኖራል። ምክንያቱም እነዚህ ተባዮች ቀን ከምሽጋቸው በመውጣት አንሶላ ላይ በመስፈር ራሳቸውን ለአደጋ የሚያጋልጡ ሞኛሞኞች አይደሉምና አንሶላን ገልጦ በማየት አልጋው ተባይ ይኑረው፣ አይኑረው ማረጋገጥ አይቻልም። አንድ የአልጋ ተከራይ ተጨማሪ እሴት (ቫት) ጭምር የተሸከመውን የአልጋ ኪራይ፣ ከ100 እስከ 150 ብር ከፍሎ በቁንጫ ሲበላ ማደሩ እጅግ አያሳዝንም? ብር ከፍሎ ለቁንጫና ለትኋን ደም መስጠት፣ ከዚያ አልፎ እንቅልፍ ማጣት እጅግ አያሳዝንም?

ለዚህም ነው አንዳንድ ሰዎች፣ ወደ መንገድ ወይም ለመስክ ስራ በወጡ ቁጥር፣ አንሶላና ደጎስ ያለ ጋቢ ይዘው የሚወጡ። አልጋ ተከራይተው ሲያበቁ፣ የአልጋ ቤቱን አንሶላም ሆነ ብርድ ልብስ አይጠቀሙም። ከተነጠፈው የቤርጎ አልጋ ላይ፣ ማለትም ከብርድ ልብሱ ወይም ከአልጋ ልብሱ ላይ የራሳቸውን አንሶላ ያነጥፋሉ፤ ጋቢያቸውን ደግሞ እንደ ላይኛው አንሶላና ብርድ ልብስም ጭምር አድርገው ይጠቀማሉ። የቆዩትን ያህል ጊዜ ቢቆዩ፣ ከመኝታ ቤት አንሶላም ሆነ ብርድ ልብስ ጋር ሰውነታቸው ሳይነካካ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ።

ለእንደነዚህ ያሉ ጠንቃቃ ሰዎች አንድ አመታዊ የሽልማት ቀን ቢዘጋጅ፣ ዋና “ስፖንሰር” የሚሆነው ማን ይመስላችኋል? “‘መንገደኞች ቢራ ሊያዘወትሩ ይችላሉ’ በሚል እሳቤ አንዱ የቢራ ፋብሪካ?” የሚል አይጠፋም። “ቢራ ፋብሪካዎች ስፖንሰርነት ይቀናቸዋል” ሲባል ስለሰማሁ፣ የዚህ አይነቱ ግምት አይከፋም። ትክክለኛ መልስ ግን አይመስለኝም። ትንፋሻቸው እስከሚያጥር ድረስ ወደ “ኢቢሲ” በመሮጥ አይናቸውን ሳያሹ ስፖንሰር የሚሆኑት የአልቤርጎዎቻችን ባለቤቶች ናቸው። የራስን አንሶላና “ብረድ ልብስ” ይዞ በመምጣት መከራየት የሚያስቀረውን አስፈላጊ ወጭ አስቡት እንጂ። የሳሙና ወጭ የለ፤ የውሀ ወጭ የለ፤ የአጣቢ ወጭ የለ፤ የአንጣፊ ወጭ የለ። ረጅሙ የአንሶላ እድሜ፣ እንደ ገና በጣም ይረዝማል። በጣም-በጣም የረዘመው የብርድ ልብሱ እድሜ እጅግ በጣም-በጣም ይረዝማል።

እርግጥ ነው እስካሁን በተጓዝኩባቸውና ባደርኩባቸው ከተሞች ውስጥ ባሉ አልጋ ቤቶች አዲስ ብርድ ልብስ ወይም ወደ አዲስ ብርድ ልብስነት ጠጋ ያለ አጋጥሞኝ አያውቅም - ሆቴሉ ወይም አልጋ ቤቱ አዲስ ካልሆነ በስተቀር። በተለይማ ከብርድ ልብሱ በላይ ጣል የሚደረግ የአልጋ ልብስ ካለ፣ ብርድ ልብሱ ረጅም ጊዜ ከማገልገሉ የተነሳ ከዳር በኩል የተቀደደ ወይም ዳርዳሩ የተበዘበዘ ሊሆን ይችላል። ይህን ሁሉ ማን አገላብጦ ያያል። ተጠቃሚው -መቼም እንቅልፍ የሞት ትንሽ ወንድም ነውና- ሌሊት እንቅልፍ ላይ እያለ አንሶላው በአንድ በኩል ጠቅለል ካለ ወይ ሲገላበጥ ወይም አለባበሴን አስተካክላለሁ ሲል፣ አንድ እግሩ በብርድ ልብሱ ቀዳዳ ውስጥ ሊገባም ይችላል። “አንዴ የተነጠፈ ብርድ ልብስ መቀየር የለበትም” የሚል መመሪያ የንግድ ፈቃድ ከሰጣቸው አካል የተላለፈላቸው ይመስል፣ ብርድ ልብሱ ባዝቶ “ዜግነቱን” እስከሚቀይር ድረስ በአዲስ አይቀይሩትም። ስለገድ የሚናገር ጠንቋይ “ብርድ ልብሱ ቢያረጅም-ቢያፈጅም እንዳትቀይሩት” ያላቸው ይመስል፣ ባዝቶ “ዜግነቱን” ካልቀየረ በስተቀር ከሆቴሉ ጋር አብሮ ያረጃታል እንጂ አይቀይሩትም።

“ብርድ ልብሱ አረጀ-አፈጀ” ብሎ በአዲስ መቀየርም ይቅር፣ ያኑ ያለውን አጥቦ የሚያውቅ አልጋ ቤት አጋጥሞት የሚያውቅ ሰው አለ? ይህን የምጠይቀው፣ ከታጠበ ከውጭ መሰጣቱ ስለማይቀር ቢያንስ አንድ ሰው ማየቱ ስለማይቀር ነው ይህን ጥያቄ ማንሳቴ። ነው ወይስ የአልጋ ቤቶቻቸውን ብረድ ልብሶች ላውንደሪ ቤት ስለሚያሳጥቧቸው ይሆን ሳናይ የቀረነው? ለቤርጎ ብርድ ልብስ ይህን አይነቱ “ቅብጠት” ቀርቶበት፣ ምናለ እቅድ ወጥቶለት (በጤና ጥበቃ ወይም በሌላ በሚመለከተው መ/ቤት) ቢያንስ በየሩብ አመቱ አንዴ ክርር ያለ ፀሀይ እንዲመታው ቢደረግ? የሚያስብ ጠፍቶ ነው እንጂ፣ እነቁንጭትና መጥፎ ጠረን ቢያንስ ለተወሰኑ ሳምንታት ሊሰደዱ ይችሉ ነበር።

ከቤርጎ ቤት ቁሳሶች ውስጥ፣ ሳይቀየር ከፍተኛ የአገልግሎት ዘመን በማስመዝገብ በኩል “ሪኮርድ” የሚሰብረው ፍራሽ ነው። ብርድ ልብስና አልጋ ሁለተኛ ደረጃን ለማግኘት ሊወዳደሩ ይችላሉ። አንደኛነትን “እናገኛል” የሚሉበት አፍ ግን የላቸውም። አቶ ትራስ “እኔም እወዳደራሉ” ካለ፣ ሳይቀየር ረጅም ጊዜ በማገልገል ለሚሰጠው የሁለትኝነት ደረጃ ሶስተኛ ተቀናቃኝ መጣ ማለት ነው። ያም ሆነ ይህ የፍራሽ ታሪክ ከሁሉም የቤርጎ ቤት መገልገያ ቁሳቁሶች እጅግ አሳዛኙ ታሪክ ሳይሆን አይቀርም። አነሰም-አደገም አንሶላ ይታጠባል - በሶስትም ይሁን በአራት ቀን ወይም በሳምነት አንዴ። ያደለው

ወደሚቀጥለው ገጽ ዞሯል

# ‘የቤርጎ ቤቶቻችን’ …

አንሶላ ደግሞ - አልጋው እስከ ተያዘ ድረስ - በየቀኑ ይታጠባል:: ትራስም ቢሆን ከአልጋው ወይም ከፍራሹ ጋር ወደ ቤርጎው ቤት ከገባ ጀምሮ፣ እንደ ፍራሹ ባይቀየርም እንኳን፣ ቢያንስ-ቢያንስ አልጋው በተነጠፈ ቁጥር የመገለባበጥ እድል አለው:: አንድ ደንበኛ ከመኝታ ክፍሉ ያለው ትራስ እንዳልተመቸው ከገለፀም፣ ከሌላ ክፍል ያለው ስለሚሰጠው፣ በዚህ አጋጣሚ ትራሶች ቢያንስ ሌላውን ክፍል የመጎብኘት እድል ይኖራቸዋል፤ “የልምድ ልውውጥ ለማድረግ ያስችላቸዋል” ባይባልም:: ፍራሽስ? ፍራሽማ ከተመደበበት አልጋ ላይ ከተኛባት የመጀመሪያዋ እለት ጀምሮ ባንድ ጀርባው እንደ ተንጋለለ እድሜውን ይፈጀታል:: ከላዩ ላይ ያለውን ነገር ለማራገፍ ያህል አንጣፊዎች በአንሶላ ጨርቅ መታ-መት ያደርጉታል፤ አለቀ፣ ደቀቀ:: ምናልባት አልጋው ከአገልግሎት ብዛት ተሰብሮ የሚጠገን ከሆነ፣ ያኔ ጀርባው ከአልጋ በመውረድ ትንሽ የመንቀሳቀስ እድል ያገኝ ይሆናል::

ሌላውና ዋናው ሳይጠቀስ ማለፍ የሌለበት፣ ምናልባትም እስካሁን ካነሳናቸው ችግሮች ይበልጥ የከፋ የቤርጎዎች ገመናም አለ - የቤርጎ ቤቶች መጥፎ ጠረን! ከመፀዳጃ ቤት ወይም ከሌላ ነገር የሚመጣ ሳይሆን፣ ራሳቸው ክፍሎቹ “የሚፈጥሩት” መጥፎ ጠረን! መጥፎ ጠረኑን እንዴ ነው የሚፈበርኩት? ወለሉ ለይስሙላ (የወዳደቀ ነገር እንዳይታይ) ያህል ብቻ “የሚፀዳ” በመሆኑ፣ ትራሱ ከተገዛ ጀምሮ በአዲስ ተቀይሮ የማያውቅ በመሆኑ፣ ብርድ ልብሱ ከተነጠፈ ጀምሮ ለአመታት ውሀ ነክቶት የማያውቅ በመሆኑ፣ ክፍሉ ሊታደስ ቀርቶ ለአመታት የግድግዳ ቀለም ነክቶት የማያውቅ በመሆኑ… ሁሉም ለረጅም ጊዜ ያጠራቀሙት የየራሳቸው መጥፎ ጠረን አላቸው:: እነዚህ መጥፎ ጠረኖች ባንድ ላይ ሲቀመሙ የምናውቀው መጥፎ የቤርጎ ቤቶች ጠረን ይፈጠራል::

ስለቤርጎ ቤቶች መጥፎ ጠረን ሳስብ፣ ከአመት በፊት መርካቶ ውስጥ፣ “አራተኛ” ከሚባለው አካባቢ የገጠመኝ ነገር ትዝ አለኝ:: እንደ እኔው በወቅቱ አዲስ አበባ ለነበረና ለምቀርበው የባህር ዳር ነጋዴ ስልክ ደወልኩ፤ በሚቀጥለው ቀን ወደ ባህር ዳር እንደምመለስ ስነግረው፣ ያረፈበት አልጋ ቤት ለአውቶቡስ መናኻሪያ ቅርብ ስለሆነ፣ እሱ ካረፈበት ሆቴል አልጋ እንድይዝ መከረኝ፤ መርካቶ ክልል ውስጥ በመሆኑ፣ ብዙ የባህር ዳር ነጋዴዎች እንደሚያርፉበት በመጠቆም ጭምር:: ምክሩን ተቀበልኩ:: ዘጠኝ ሰአት አካባቢ ሻንጣዬን ይዤ ወደ መኝታ ቤቱ አመራሁ:: ሂሳቡን ከነ”ቫቱ” ከከፈልኩ በኋላ፣ ቁልፍ ተቀብዬ ወደ መኝታ ክፍሌ ሄድኩ፤ ከፈትኩ:: ሆኖም እንደ አካሄዴ ዘው ብዬ መግባት አልቻልኩም:: ከውስጥ አየሩን እየተጋፋ የሚመጣው የመኝታ ክፍሉ መጥፎ ጠረን ባለሁበት እንድቆም አደረገኝ:: ይሄውላችሁ - ብዙዎቹ አልጋ ቤቶች፣ በተለይም እድሜ ያስቆጠሩት፣ ይህን ያህል በሚከረፋ ጠረን ተበክለዋል…

ንጋት ላይ ቁም ሳጥኑን ከፈትኩ - ከውስጡ ያሳደርኩትን ጃኬት ለለብስ:: ጃኬቱን ገና ትከሻዬ ላይ ጣል በማድረግ፣ ልለብስ ስል ትናንት ከበሩ ላይ ያገተኝ መጥፎ ጠረን አጠነኝ:: ነገሩ በጣም ስለገረመኝና ይበልጥ ማረጋገጥ ስለፈለኩም ጭምር ጃኬቱን ወደ ፊቴ ዘወር በማድረግ አሸተትኩት:: ትክክል! ሚስኪን ጃኬቴ በአልቤርጎ መጥፎ ጠረን ተበክሏል:: የጠረኑ ጥንካሬ፣ ያለ ማጋነን፣ እንደ ”ፍሊት” ያን የክፍሉን መጥፎ ጠረን ሆን ብለው የረጩበት ይመስላል:: ጃኬቴን ከቁም ሳጥኑ ውስጥ ማሳደሬ እየቆጨኝ፣ ባለ ሀይሌ ደጋግሜ አራገፍኩት:: ሌላ ምን ምርጫ አለኝ:: አድሎት ፈረንጅ ቢገዛው ኖሮ የሳልባጅ ጨርቆችን ለመቀላቀል እድሜው ባያንሰውም መጣል እሚባል ነገር በልቤ ውልም አላለኝ:: ደግሞስ ከዚያ ክፍሉ ብቻ ሳይሆን ከውስጡ ያለው ቁሳቁስ ጭምር ከሚከረፋ መኝታ ቤታቸው ስላሳደሩኝ ሽልማት መሆኑ ነው ጃኬቴን ጥዬላቸው የምሄድ::

ምሽት ላይ ከነጋዴው ጓደኛዬ ጋር እንደ ተገናኘን፣ ሰባራ ወፍ እንኳን ሳትቀድመኝ ስለክፍሉ መጥፎ ጠረን ነገርኩት:: እርግጥ ነው፣ ወደ እሱ ክፍል ስገባም ተመሳሳይ ጠረን ስለሸተተኝ የዚያ ሆቴል መኝታ ቤቶች ችግር መሆኑ ገብቶኛል:: እናም ይበልጥ ወደ ምከሩ አዘነበልኩ:: ለንግድ ስራው ቶሎ-ቶሎ ወደ አዲስ አበባ ስለሚመላለስ፣ የቤርጎ ቤቶቹ መጥፎ ጠረን ከእድሚያቸው/የአገልግሎታቸው ጊዜ ብዛት ጋር ጭምር ስለሚገናኝ መርካቶ አካባቢ ከሚያርፍ በጎጃም መውጫ በኩል አዳዲስ ሆቴሎች ስላሉ ፊቱን ወደ እዚያ እንዲያዞር መከርኩት::

ምክሬን ተቀብሎ ለሁለት ጊዜ ያህል ምሽት ላይ እየሄደ ጎጃም መውጫ አካባቢ ካለ አንድ ሆቴል አልጋ እንደ ያዘ፣ በአልጋው አገልግሎት መርካቱን ነገረኝ:: አንድ እለት፣ ከቀኑ ስምንት ሰአት አካባቢ ለሶስተኛ ጊዜ ለተመሳሳይ አገልግሎት፣ ማለትም አልጋ ለመከራት ወደ እዚሁ ሆቴል አመራ:: ደክሞታልና አረፍ ማለት ይፈልጋል:: ሂሳቡን በመክፈል፣ አልጋ ተከራየ፤ የተከራየው አልጋ ቁጥር ተነገረው:: ሆኖም የሆቴሉ አልጋ አከራዮች የአልጋውን ቁልፍ ሊሰጡት ፈቃደኛ አልሆኑም:: ቁልፉ የሚሰጠው ከምሽቱ አንድ ሰአት በኋላ እንደ ሆነ ተነገረው:: አልጋ ተከራይቷል፤ አልጋ ግን የለውም::

ግን ለምን? ምክንያቱም የሆቴሉ አልጋዎች በሙሉ ቀን-ቀን “ለድብቅ ፍቅረኞች” (ለዝሙተኞች) አገልግሎት ይሰጣሉ:: የዚህ አይነት ተገልጋዮች ደግሞ እንዳፈር ናቸው:: ስለዚህ አንድ አልጋ፣ በአንድ ቀን-ሌሊት የሚተኛበት ሰው ሳይቆጠር-ለሁለት፣ ለሶስት ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ዝሙተኞች አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል:: መሰል ሆቴሎችም፣ የተንገበገቡለትን ገንዘብ በስንጥቅ ትርፍ ያፍሳሉ - ለዚያውም ያለ ቀረጥ:: ይህን የምለው፣ መቼም የፈለጉትን ያህል ሀቀኛ ሁነው ቢሞቱ “‘አልጋዎቻችንን ሌሊት ከሚያድሩባቸው ሰዎች በተጨማሪ ቀን፣ ቀን በዝሙት ለሚባልጉ ሰዎችም አከራይተናል’ በማለት ግብር ይከፍላሉ” ብሎ ለማሰብ ስለሚከብድ ነው:: ዞሮ ዞሮ ይህም ሌላው የቤርጎ ቤቶች ገመና ነው - ደንበኛን ከማጉላላት አልፈው ተርፈው ዝሙትን የገቢ ማስገኛ መንገድ አድርጎ መያዝ:: ግን-ግን ባለሆቴል ቤቱ፣ ሚስቱ ወይ ልጁ ሌላ የሆቴል ባለቤት ባመቻቸው አልቤርጎ የዝሙት ተግባር ላይ ብትሰማራ ደስተኛ ይሆናልን? ባለሆቴል ቤቷ፣ ባለቤቷ ወይም ልጇ ሌላ የሆቴል ባለቤት ባመቻቸው አልቤርጎ የዝሙት ተግባር ላይ ቢሰማራ ደስተኛ ትሆናለችን?

ከዚህ አንፃር፣ እርግጥ ቁጥራቸው እጅግ ውስን ቢሆንም፣ ዝሙትኝነትን በራሳቸው አቅም እየታገሉ ያሉ አንዳንድ ቤርጎ ቤቶችም አሉ፤ ሊሞገሱ የሚገባቸው:: አንድ ሰው ሚስቱ ከሆነች ወይም አንዲት ሴት ባሏ ከሆነ ሰው ውጭ በአንድ አልጋ ላይ አብረው ማደር አይችሉም::

የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለሁ፣ “የኮመርስ” መምህራችን የአልቤርጎ አገልግሎት እጅግ በጣም አዋጭ የንግድ ዘርፍ መሆኑን እንደ ነገረን አስታውሳለሁ:: “ባለአልጋ ቤቱ አንዴ ለአልጋ ቤቱ የሚያስፈልገውን ቁሳቁስ ካሟላ በኋላ፣ ያለበት ወጭ ሳሙናና ውሀ ብቻ ነው” እንዳለንም አስታውሳለሁ:: ይህ ማለት ግን እጅግ የሞተ አገልግሎት እየሰጡ፣ ተጠቃሚውን ይሞጭልፉት አለማለት መሆኑን እረዳለሁ:: ከብዙዎቹ የአገራችን አልጋ ቤቶች አንፀር አሁን ያለውን አገልግሎት በደምሳሳው ለገመገመ ሰው፣ እንደ አልቤርጎ ተጠቃሚ የተንገላታ፣ የተበደለ፣ በከፈለው ገንዘብ ስቃይ እንዲገዛ የሚደረግ ተገልጋይ ያለ አይመስለኝም::

የአገራችን ቤርጎዎች እንደ አሸን የፈሉ የመሆናቸውን ያህል፣ ብዙ-ብዙ ችግሮች አሉባቸው:: ብዙዎቹ ችግሮች ደግሞ ተመሳሳይ ናቸው:: ይህ ሁኔታ ችግሮቻቸውን በማጥናት በዘላቂነት ለመፍታትና ተገልጋዩ ህዝብ ለከፈለበት ቤርጎ ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ ለማድረግ ያስችላል፤ ለምሳሌ ለቤርጎ ቤቶች ደረጃ ማውጣትና የቁጥጥር ስርአት መዘርጋት አንዱ የመፍትሄው አካል ሊሆን ይችላል::

በነገራችን ላይ ፈቃድ የሰጠው አካል ለምን ይሆን አልጋ ቤቶችን እንዲህ መረን የለቀቀብን? ጤና ጥበቃዎች ለምን ይሆን ይህን ሁሉ የመኝታ ቤቶች ጉድ እያዩ እንዳላዩ የሚሆኑት? ነው ወይስ እነሱ አይተኙባቸውም? ነው ወይስ አብዛኛዎቹ የነሱና የወገኖቻቸው ናቸው? ነው ወይስ…

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል:: እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን::

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በአድራሻችንና በኢሜል መላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን::

ዝግጅት ክፍሉ

# የማሕበረሰብ አገልግሎት የልምድ ልውውጥ ...

ከገጽ 8 የዞረ

## ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ

ከላሊበላ ጉብኝት በኋላ ጉዞ ወደ ወልደያ ዩኒቨርሲቲ በማድረግ ወልዲያ ከተማ አመሻሽ ላይ ደረስን፡ ፡ ወልዲያ ከአራት አቅጣጫዎች የየብስ ትራንስፖርት የሚበዛባት ከተማ በመሆኗ የደረቅ ወደብ ከተማ አስብሏታል፡፡

ወልድያ ዩኒቨርሲቲው በደረስንበት አጋጣሚ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር የማሕበረሰብ አገልግሎት ለመስጠት ከማሕበረሰብ ተወካዮች ጋር እያደረገ ነበር፡፡ ተወካዮቹ ልጆቻቸው በሚማሩበት ዩኒቨርሲቲ ተገኝተው ከዩኒቨርሲቲው ኃላፊዎች ጋር ያሉባቸውን ችግሮች በጋራ ለመፍታት የሚያደርገው ጥረት ዩኒቨርሲቲው ምን ያህል ወደ ማሕበረሰቡ እንደገባ መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ለቡድኑ የተለየ ልምድ የሆነው ከአረብ ሀገራት የተመለሱ ስደተኛ ሴቶችን የኢንተርፕነርሽፕ ስልጠና በመስጠትና በማደራጀት ወደ ስራ አሠማርቷል፡፡ ሌላው ትኩረታችንን የሳበው በሀገር በቀል እውቀት በተለይ በባሕል መድኃኒት ላይ የተደረገ ምርምርና ማሕበረሰብ አገልግሎት ነው፡ ፡ ከባሕላዊ መድኃኒት ቀማሚዎች ጋር በመቀናጀት ባሕላዊውን አሰራር ወደ ሳይንሳዊ ለመለወጥ የተካሄደው ስራ ውጤታማ መሆኑን ቡድኑ ተገንዝቧል፡፡

## መቀሌ ዩኒቨርሲቲ

መቀሌ ለመሄድ የግራካዕን ተራራ መውጣት ይጠበቅብናል፡፡ የግራካዕ ተራራ ጠመዝማዛ መንገድ በማለፍ መቀሌ ከተማ ደርሰናል፡፡ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ አብርሃወ አፅብሃ በተባለ የገጠር ቀበሌ የተሰራው ልማትና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ የቡድኑን ቀልብ ከሳበው ስራ ዋነኛው ነው፡ ፡ የአካባቢው ሕብረተሰብ ክረምትን ጠብቆ የሚያመርት የነበረ ሲሆን አሁን ግን ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በመስኖ አማካኝነት የአካባቢውን ማሕበረሰብ ተጠቃሚ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ሌላኛው የማሕበረሰብ አገልግሎት ትኩረትየተሰጠውስራየዩኒቨርሲቲው ጤና ኮሌጅ "የሀይደር ሪፈራል ሆስፒታል" ነው፡፡ የኮሌጁ እጩ ተመራቂና መምህራን በሆስፒታሉ ሙያዊ የማሕበረሰብ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡ ኮሌጁ ለሌሎች ሆስፒታሎችና ጤና ተቋማት የሙያና ቁሳቁስ ድጋፍ ይሰጣል፡ ፡ ሀይደር ሆስፒታል ከተቋቋመ 11 ዓመት ቢሆነውም በሀገር ደረጃ ሁለተኛው ትልቁ ሆስፒታል ነው፡ ፡ ሆስፒታሉ በአካባቢው ሳይወሰን ለጐንደር ዩኒቨርሲቲም የህክምና መሣሪያ ድጋፍ አድርጓል፡፡ በሀይደር ሆስፒታል ከፍለው መታከም ለማይችሉ የማሕበረሰብ ክፍሎች ነፃ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ሕክምና ኮሌጁ በህፃናት አስተዳደግና አያያዝ፣ በስነ ተዋልዶና በአባለዘር በሽታ ከመቀሌ የማሕበረሰብ ሬድዮ አየር በመግዛት ትምህርት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በመቀሌ ለሚገኙ ሴተኛ አዳሪዎች ስለ አባላዘር በሽታና ኤች አይ ቪ ኤድስ እያስተማረ ነው፡፡ በተጨማሪ ኮሌጁ በሀገሪቱ የመጀመሪያ የሆነውን ኦክስጅን እያመረተ ለገበያ ለማቅረብ ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡

## ለአክሱም ዩኒቨርሲቲ መድረሻ

ከመቀሌ ተነስተን የአብርሃ ወአፅብሃ የልማት ቀበሌ ጉብኝተን ጉዞ ወደ አክሱም ከተማ፡፡ አክሱም ከመድረሳችን በፊት የኢዛና እና ሳይዛና የተባሉ ነገስታት የሰሩት የተራራ ውስጥ ፍልፍል ቤተክርስቲያን ይገኛል፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ ስም አብርሃ ወአፅብሃ ይባላል፡፡ ኢዛና እና ሳይዛና መንትያ ወንድማማች ሲሆኑ አብርሃ ወአፅብሃ በንግስናቸው የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ ይህ ገዳም በ320 ዓ.ም በመጋቢት ወር የተጠናቀቀ ሲሆን በዩዲት ጉዲት ዘመን ቃጠሎ ደርሶበታል፡፡ የገዳሙ ውስጠኛው ክፍል የሚያንፀባርቅ ብርሃን እንደነበረው አስጐብኛችን የገለጹልን ሲሆን በዩዲት ጉዳት ቃጠሎ የደረሰበት ቢሆንም ቃጠሎው ጥሎ ካለፈው የቃጠሎ የሚመስል ጥቁር አሻራ ውጭ በእድሜ ብዛት የሚታዩ የመሰንጠቅና የመጐዳት ምልክት አይታይበትም፡፡

ቀጣይ ጉዟችን ጥንታዊው የአልነጃሽ መስጊድ ነው፡፡ አልነጃሽ በንጉስ ነጋሽ ዘመን ነብዩ መሐመድ ወደ አቢሲኒያ የላኳቸው የእስልምና እምነት ተከታታዩች በእንግድነት በመቀበላቸው ለእሳቸው መታሰቢያ የተሰራ ነው፡፡ መስጊዱ ጥንታዊ ሲሆን የንጉስ ነጋሽ እና ወደ አረብ ሀገር ያልተመለሱ የእምነቱ ተከታዮች መቃብር ይገኝበታል፡ ፡ በአሁኑ ወቅት መስጊዱ በቱርክ የኮንስትራክሽን ድርጅት እድሳት እየተደረገለት በመሆኑ ቡድኑ ለጉብኝት ወደ ውስጥ መግባት ባለመቻሉ ቅሬታ ቢያድርበትም በሌላ ጊዜ ጉብኝት ይህንን ታሪካዊ ቦታ ለመጎብኘት ቀጠሮ በመያዝ ጉብኝታችንን ቀጠልን፡፡

በመቀጠል ጉብኝት የተደረገው ደብረዳሞ ገዳም ነው፡፡ ይህ ገዳም አቡነ አረጋዊ በተባሉ አባት የተመሰረተ ነው፡፡ አቡነ አረጋዊ የሮም ንጉስ ልጅ ሲሆኑ በ14 ዓመታቸው የምንኩስናን ስልጣን አግኝተው የምንኩስና ዘመናቸውንም በኢትዮጵያ እንዳሳለፉ ተረድተናል፡፡ ደብረዳም ገዳም ከጭቃና ከድንጋይ የተሰራ ሲሆን 1530 (አንድ ሺ አምስት መቶ ሰላሳ) ዘመን አስቆጥሯል፡፡ ገዳሙ በየትኛውም አቅጣጫ የመግቢያና መውጫ በር ባለመኖሩ ወደ ገዳሙ ለመግባትና ለመውጣት ከጫፍ ከተራራው ወደታች በተዘረጋ ጠፍር መውረድና መውጣት ግድ ነው፡፡ በገዳሙ ዙሪያ ላይ 150 የማይነጥፉ የውሃ ጉድጓዶች ሲገኙ የ150 ጥንታዊ አባቶች መቃብር ይገኝበታል፡፡

## አክሱም ዩኒቨርሲቲ

በአክሱም ዩኒቨርሲቲ የተለየ የማሕበረሰብ አገልግሎት በወጣት ታራሚዎች ላይ የሚሰራው ስራ ነው፡፡ በአክሱም ከተማ ማረሚያ ቤት ወጣት ታራሚዎች የእስር ጊዜያቸውን አጠናቀው ሲወጡ ውጤታማ መሆን የሚያስችላቸውን ስልጠና በመስጠት እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ዩኒቨርስቲው ከፍተኛ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡

## ጐንደር ዩኒቨርሲቲ

ጉዟችን ከአክሱም ወደ ጐንደር ዩኒቨርሲቲ ለመሄድ መዳረሻችን ወደ ሆነችው ወደ ሑመራ ከተማ ቀጠለ፡፡ የሑመራ ከተማ በአሸዋማው መሬት የተከዜን ወንዝ በመንተራስ ከኤርትራ ማዶ ትገኛለች፡፡ ቡድኑ ሑመራ የደረሰው ሙቀቱ በሚበረታበት ከሰዓት ቢሆንም ከተማዋን ለመጎብኘት ግን አላገደንም፡፡ ሑመራ ምንም እንኳን ብርቱ የሆነ ሙቀት ያለባት ብትሆንም ያደገችና ሞቅ ያለች ከተማ ናት፡፡

ከሁመራ በቀጥታ በጠዋት የገሰገስነው ወደ ጐንደር ከተማ ነው፡፡ በጐንደር ከተማ የሚገኙትን ጥንታዊ ቅርሶችን ለመጐብኘት በጠዋት መነሳት ግድ ነበር፡፡ በ26ኛው ክፍለ ዘመን የተሰራውን የአፄ ፋሲል ቤተ መንግስት በ70 ሺህ ካሬ ሜትር ተንጣሎ ይገኛል፡ ፡ በዚህ ግቢ ገብተንም ታሪክን ወደኋላ በአይነህሊናችን እየተጓዝን በግቢው ውስጥ የሚገኙትን ስድስት ቤተ መንግስቶች ጎበኘን፡፡ አፄ ፋሲል በ1631 ቤተመንግስታቸውን በማስገንባት የመናገሻ ከተማ በማድረግ እስከ መጨረሻ ዘመናቸው በጐንደር ኖረዋል፡፡

በጐንደር ዩኒቨርሲቲ የማሕበረሰብ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ትኩረታችንን የሳበው ማንኛውም መምህር ከመደበኛ ስራው 15%ቱን ለማሕበረሰብ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት የሚደነግግ ፖሊሲ ተቀርጾ እየተንቀሳቀሰና ለተግባራዊነቱም ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝ ማወቅ ችለናል፡፡ አንጋፋው የጐንደር ዩኒቨርሲቲ ህክምና ኮሌጅ ከፍለው መታከም ለማይችሉ የማሕበረሰብ ክፍሎች ፕሮጀክት በመቅረጽ ታካሚው ወዳለበት ቦታ በመሄድ የአይን ሞራ ግርዶሽ ገፈፋ እየሰራ ይገኛል፡፡ እንግዲህ ጉዟችን ባጭሩ እንዲህ ይመስላል፡፡

እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# "Success is walking from failure to failure with no loss of enthusiasm"

**(Winston Churchill)**

**Yenus Nurie (Department of English Language and Literature)**

Since we automatically assume that things will go alright because everyone is responsible, we often directly rush towards the practice before evaluating ourselves if we are well prepared and adjusted to new policies and strategies as success requires a determined effort to cope with setbacks. Indeed, success requires responsibility, yet the fruit of responsibility ripens if only we realize our personal commitment and have the courage to pursue our visions. My genuine sense of concern in this paper is, therefore, to suggest that while it is a commonly held belief that to try leads to success for whatever we intend to do, we should first create a sense of movement to a more motivating and inspiring thoughts.

To begin with, a few years have passed since our university set its goals, created its visions, and utilized its maximum effort to attain the desirable outcome. In these inspiring messages, every one recognized how deeper the purpose of the work will be, and has been struggling on their part to knock out this massive goal and reach it. Similarly, the university has been working aggressively in facilitating, scaffolding and supervising the whole progresses of this project. However, as working hard can lead to achievement, recognizing and overcoming the common pitfalls that could potentially destroy the motivation and spirit of the staff, and consequently lag the success helps us not only to avoid the drift situation but also to devise and implement the mission more confidently in the future.

It is an established fact that we may encounter multiple stranded pitfalls in carrying out the project. Nevertheless, I strongly believe that having little or no motivation and negativity play the most embarrassing blunder by undermining our enthusiasm and spirit. On the other hand, motivation and positivity are the most essential spices of success. Worded differently, effective attitudes and actions employed by teachers absolutely can make a positive difference on the lives of their students and the broad mission of their university, and it is this belief that initiates me to reflect on how the university has to collaboratively work with instructors to meet their common objectives, and this is the central focus of this paper.

Peer-led learning is a new core component in Ethiopian Universities and its aim is to produce students who are socially and academically competent citizens so that they contribute much to the development of their country. In practical terms, by engaging students in doing tasks with their peers, it is assumed to be serving as a milestone for a variety of purposes such as scaffolding weak students, improving of the existing insufficient students' interpersonal competence and fostering their academic abilities, and hence improving quality education.

As an academic advisor, I have been working for almost three years, but honestly speaking apart from the conventional academic tasks, I don't dare to deserve mentoring these students on the newly emerging peer-led group formation. Although I am part of the team, it has been hard for me, for I did not understand well of peer-led learning and I had confusions to implement it effectively. On the whole, despite the fact that peer-led approach has got momentum in various areas of the world, it has increasingly been recognized that learners and instructors' attitude is not playing a vital role in advancing the future aspirations of the university. Actually, this problem should be considered in relation to lack of sufficient training on the pedagogical and managerial practices of this new learning technique.

On the one hand, involvement in peer-led learning is seen as central to promote students' overall development. Hence, this involvement necessarily requires attention and attitude of all stakeholders, students and instructors. Unfortunately, I claim that this scientific technique does not appear to have been implemented as it needs to have been. In a nut shell, clear and meaningful reconsiderations should be taken to see our vision come true. Thus, unless scrupulous and meaningful steps to develop positive attitude towards the package are taken to aid students' learning, regrettably I doubt that our ambition to pursue the noble vision will be hampered if not destroyed.

**It is through mutual construction of grouping, assessing and supervising all students that we can engage active participants in the process**

Bearing this caveat in mind, I would like to state ways that help deliver positive motivation of students and to equip teachers with a responsive attitude. It seems that teachers' attitude toward peer-led learning derives not only from their self-image as teachers but also from the perception they have of the benefit of peer-led learning in their specific subject. People with strong negative feelings toward peer-led learning may avoid practicing it even if they are expected to do so. On the other hand, when teachers have a positive disposition toward peer-led learning, they are more prone to seek and apply teaching strategies that promote their subject, even if they have low know-how. The university management and administrators should keep these elements in mind when they select and appoint mentors. Through regular reflections upon such factors teachers can be enlightened as to the affective foundations of their teaching, and only then can they successfully make the necessary adjustments to improve their practice.

With regard to students, it is clear that students do value peer-led learning for guidance, countering a concern mentioned before. Indeed, most of the students cared about peer-led learning and want to benefit from it to make further improvements. However, in reality, it was observed that the existing peer-led learning, which only academically active students participating did not enhance their academic advancement. Teachers should consult mentors in grouping students and giving assignments for their students, and work together with academic advisors. In sum, it is through mutual construction of grouping, assessing and supervising all students that we can engage active participants in the process, and thereby succeeding our mission.

Guided by this core principle which leads to mark an important and ambitious shift in revivifying students' attitude towards peer-led learning practices, we can genuinely facilitate our students' progress in learning. It is; therefore, important to recognize that students' perspectives towards peer-led learning is crucial as students' ability to learn from it relates to their capacity to make sense of and apply peer-led learning to foster their learning. This can be achieved by employing a variety of techniques. We have to enrich students' and teachers' general motivation about peer-led learning. For example, persistent workshops and experience sharing seminars for teachers and students should be held. The university needs to promote better understanding and development of attitudes by encouraging teachers to conduct research and disseminate their papers on issues related to the practices and challenges of practicing peer-led learning.

To round up, although teachers are supposed to recognize how vital peer-led learning will be to supplement learning and teaching, they seem to fail short of giving clearly communicated expectations and mentoring in the way it should be. Based on my everyday observations, mentors' actual practice in viewing and experiencing this reality and their reactions to it are remarkably lacking. Thus, it is the right time for the university management to persistently create awareness on the essence of peer-led learning and train both students and teachers as success is measured by only on the approval of thoughtful and committed individuals who can genuinely adjust and manifest their inspirations.

# ቄንጠኛው (ልብወለድ) ክፍል 8

ከባለፈው እትም የቀጠለ


አረጋዊ ሰለሞን AS (3ኛ ዓመት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ተማሪ)

Aregawisolo27@gmail.com


ማክሰኞ 07:40

ፀሐይ የፍጥረትን አናት ለመብሳት የቋመጠች ትመስላለች፡፡ ምድር ከታች ወደላይ በጉልበት የምትተፋው የጋለ እንፋሎት የተማሪዎችን ገፅ ይለበልባል፡፡ ጥቂት ጥላማ ቦታ ላይ ከተቀመጡት ውስጥም የሚያንቀላፉ አልጠፉም፡፡ ከዋናው ግቢ የመሰብሰቢያ አዳራሽ (ኦዲትሪየም) ፊት ለፊት የቆሙ መኪኖች ከፀሐይቱ የመጣላቸውን ጨረር ላለመቀበል በመቃወም መልሰው ወደየአቅጣጫው ይበትናሉ(ያንፀባርቃሉ)፡፡

ክፍል ውስጥ ተቀራርበው የተቀመጡት ተማሪዎች እንቅልፍ ሰልጥኖባቸዋል፡፡ ፊታቸው ላይ የድብርትና የድካም ስሜት በጉልህ ይነበባል፡፡ ከመማር ይልቅ እንቅልፍን አስመኝቷቸዋል፡፡ ይህን የተረዱት መምህር ጌትነት ተማሪዎቹ ተበታትነው እንዲቀመጡ ካደረጉ በኋላ በጠመኔ በነጡት ጣቶቻቸው መካከል የጠቋሚ ጣታቸውን ወደ ጥግ በመቀሰር «አንተ ማነህ ጥግ ያለኸው ና ወደዚህ፡፡» ቄንጠኛውን፡፡

ቄንጠኛው ከወትሮው በተለየ መልኩ ሁኔታው ተቀያይሯል፡፡ በልኩ ተመጥኖ የተሰራ አዲስ ጫማ ተጫምቷል፡፡ ሱሪው እንደወትሮው የሁለት ሰው (ሰፊ) አይደለም፡፡ በውስጥ የለበሰው 'ፓንት' በሱሪው ተሸፍኗል፡፡ የትናንቱ ጨበሬው ፀጉሩ ዛሬ ከቄንጠኛው ጋር የለም፡፡ የሲጋራ ወልፉን ለማስታገስ ብሎ የገዛትን ማስቲካ በመንጋጋው ጫን ለቀቅ ያደርጋል፡፡ «እኔን ነው ቲቸር?» አለ መምህሩ የጠሩት እንደሆነ ለማረጋገጥ፡፡

«አዎ አንተን ነው፡፡ ና እስቲ ወዲህ፡፡» አሉት መምህሩ፡፡ ቄንጠኛው ከተቀመጠበት ተነስቶ ከመምህሩ ፊት ለፊት ቆመ፡፡

«ማነ ነበር ስምህ?» አሉትና «ይቅርታ ስምን ሸምድዶ መያዝ ስለማይሆንልኝ ነው፡፡»

«አይ ጣጣ የለውም፡፡ አቤል እባላለሁ፡፡» አለ ቄንጠኛው ራሱን ቁልቁል ደፍቶ፡፡

«አቤል ምን ተገኝና ነው ዛሬ ሽክ ብለህል?»

«ኧረ ምንም አልተገኘም፡»

«እና ያ ምን የመሰለውን ፀጉርህ ቆርጠህ ጣልከው?» አሉት በሽሙጥ፡፡

«ምን ያደርጋል ብለው ነው ቲቸር?» አለ እየተቅለሰለሰ፡፡

«እንዴት? ምንም ሣያደርግ ከሆነ እንዴት 3ት አመት ያክል አብሮህ ዘለቀ?»

«ካሳለፍኳቸው ጊዜያት ውስጥ አንዷም እንኳን ለራሴ ኖሬያት አላውቅም፡፡ የሆነ ነገር ከማድረጌ በፊት ጀለሶቼ ምን ይሉኛል ነበር የምለው፡፡ አሁን ግን አንድን ነገር ከማድረጌ በፊት ለምን? ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ፡፡ በነገራችን ላይ አያና በሕይወቱ ባይሰብከኝና ይችን መፅሐፍ ባይሰጠኝ ኖሮ እንዲህ አልሆንም ነበር፡፡ ምክንያቱም ለራስህ ጊዜ መስጠት ትልቅ ነገር ነው ብዬ ስለማምን፡፡ እያንዳንዳችን ማወቅ ያለብን ነገር ቢኖር መለወጥ ከራስ መጀመር እንዳለበት ነው፡፡ እንዲህ አድርግ ብሎ የሚመክር ሰው ብዙ ቢሆንም የሚተገብር ግን በጣም ጥቂት ነው፡፡ ለማንኛውመ አያናን አመሰግናለሁ፡፡» አለ ቄንጠኛው በኋላ ኪሱ ውስጥ የነበረችው የዴል ካርኒጌ ጠብታማር መፅሐፉን አውጥቶ፡፡

«እንግዲህ ሱሪ ዝቅ ማድረግ ምናምን የለም ማለት ነዋ?»

«አዎ ቲቸር No more slave. ድሮም ነፃ ነበርኩኝ አሁንም ነፃ ነኝ፡፡ ባለውለታዬ ኖት፡፡»

«መልካም፡፡ በል ተቀመጥ፡፡... አያችሁ መለወጥ እንዲህ ነው! በርታ ለላይኛው ውበታችን በተጨነቅን ቁጥር ውስጣችን ባዶ እየሆነ ነው የሚሄደው፡፡ .... እሺ ለዛሬ እዚህ ላይ እናብቃ፡፡ መሄድ ትችላላችሁ፡፡» አሉና ተማሪዎቹ እንዲወጡ ተፈቀደላቸው፡፡

«ሄለው፡፡ የት ነህ?..... አሁን ከ Class እየወጣሁኝ ነው፡፡» አለች ትዕግስት

«እኔም ከ'ክላስ' እየወጣሁኝ ነው፡፡ አሁን መገናኘት እንችላለን?» አላት ቄንጠኛው፡፡

«እያየሁህ ነው ጠብቀኝ፡፡» አለችው ትዕግስት ከጆኮ ግቢ ህፃን ላይ ሆኗ ቁልቁል እየተመለከተች፡፡

ልክ ካጠገቡ እንደደረሰች «ወይኔ እንዴ ታባህ እንዳማረብህ! አሁን ወንድ መሰልክልኝ፡፡» አለችና ከንፈሩን እንደመቅመስ ሳም አደረገችው፡፡

«የምርሽን ነው የኔ ፍቅር አምሮብኛል?»

«እንዴ በጣም ነዋ! በዛ ላይ ደግሞ ንፍቅ ብለኸኝ ስለነበር ነው መሰለኝ ጉረሸው ጉረሸው እስኪለኝ ድረስ ነው የናፈቅኸኝ፡፡» አለችው፡፡

«እና ለምን አትጉርሽኝምና አይወጣልሽም?»

«አይ እኔማ መቼም ቢሆን የሚወጣልኝ አይመስለኝም፡፡»

«እኔ እምልሽ ማር ሽማግሌ ልላክ እንዴ?»

«ወዴት?»

«ወደ ቤታችሁ ነዋ፡፡ አሁን ቶሎ ብዬ አንቺን ማግባት እፈልጋለሁ፡፡»

«ከዛስ?»

«ከዛማ አንድ ላይ ሆነን በሰራናት ቤት ላይ በረንዳው ላይ ሆነን ቀሚስሽን ለብሰሽ፣ ሳር ጎዝጉዘሽ ቡና አፍልተሽ እየጠጣን ልጆቻችን ሲስቁና ሲሯሯጡ እናያለን፡፡»

«አባዬ እኮ ሃይለኛ ነው፡፡ በቀላሉ እሺ አይልም፡፡ እምቢ ቢልስ?»

«ደጋግመው እንዲለምኑልኝ ሽማግሌዎችን እልካለሁ፡፡ እምቢ ከሆነ ግን ይዤሽ እልም ብዬ እጠፋና አብረን እንኖራለን፡፡»

«ለምን አሁን ይዘኸኝ አትጠፋም?»

«አሁን እማ ከእኔ ጋር እንዳትሆኚ የሚከለክልሽ የለማ፡፡» ብሎ ከንፈሯን በከንፈሩ.......፡፡

«ቲያትራችሁ ምን ላይ ደረሰ?» አለችው ትዕግስት ዓይን ዓይኑን እያየች፡፡

«አርብ እናሳየዋለን በለን አስበናል፤ ቢሮክራሲው ካላስቸገረን፡፡የፖስተር ዲዛይኑ ተጠናቋል፡፡ ፀሐይዋ ቀዝቀዝ ስትል እንለጥፈዋለን፡፡» አለና ቄንጠኛው መለሰላት፡፡

«እና አትጋብዙኝም እንዴ?»

«እንዴ ቀላል እጋብዝሻለሁ! ለዚያውም አሪፍ ቦታ ላይ ሆነሽ እንድታይው ነው የማደርግሽ፡፡»

«Thank you የኔ ማር!» አለችና ደግማ ከንፈሩን ሳመችው፡፡ የፍቅር ወሬአቸውን እየኮመኮሙ ዶርሟ ድረስ ሸኝቷት ተመለሰ፡፡

አያና በቲያትሩ ዝግጅት ምክንያት እረፍት አጥቷል፡፡ ሀሳቡ ሁሉ ቲያትሩ ላይ ሆኗል፡፡ አብመላሽና ኤርሚያስም ከአያና ጋር ሆነው ውርውር እያሉ ነው፡፡

ፖስተሮቹ የት የት አካባቢ መለጠፍ እንዳለባቸው፣ እነ ማን ቅድሚያ መጋበዝ እንዳለባቸው፣ ቲያትሩም ስንት ሰዓት መታየት እንዳለበት ተወያይተው በወሰኑት መሰረት ፖስተሮቹ ለሁሉም እንዲታዩ በማሰብ አንዱን ኦዲትሪየም ጋር ሁለተኛውን ደግሞ ከFBE DSTV ፊት ለፊት ተለጥፏል፡፡ የመጥሪያ ካርዶችም ተዘጋጅተው ጨርሰዋል፡፡

ቄንጠኛው ለዕለቱ የሚሆኑ ተጨማሪ ዝግጅቶችን ለማቅረብ ልምምድ እያደረገ ነው፡፡ ሁሉም በስራ ተጠምደዋል፡፡ ድካማቸውም የተሳካ እንዲሆን ቆርጠው ተነስተዋል፡፡ ሁሉም ዓርብን በጉጉትና በጥረት እየጠበቋት ነው፡፡

ማስታወሻነቱ ለነሰሎሞኖች ይሁንልኝ፡፡

**ይቀጥላል!!!**

# የ ግ ጥ ም ጥ ግ

## እራስ ወዳድ ፍቅር

ጽዕኑ አፍቃሪ ሴት፣ ልክ እንደ ሰብለ  
የማይበገር ወንድ ፣በዛብህ የት አለ?  
ለፍቅር ተሚጋች ፣ጉዱ ካሳን ያክል  
ተራራ የሚንድ የአኗኗር ይትባህል  
በፍቅር የመነነ፣ን የ፣ሚቀበል ደብር  
ለፍቅር የሞተን የሚያለብስ አፈር  
የለም ይላል ሰው  
ይህን የሚለው፣ ሰው የግል ፍላጎቱ  
ፈላስፋ ያደረገው ፣የህልም ሰገነቱ  
በፍቅር እንኑር  
በፍቅር እንቀበር  
እያለ የሚሰብከው  
እራስ ወዳድ ሰው ነው  
እኔ ግን እላለሁ  
ቀድሚያት፣ ከሞትኩኝ  
ሌላ ሰው ፣አታፍቅር  
እኔን እያሰበች ፣በምናኔ ትኑር  
እጣን ጧፍ አብርታ ፣  
ፍቅራችንን ትዘክር  
ቀድማኝ ፣ከሞተች ግን  
ለብቻየ መሆን ፣እፈራለሁና  
እሷን ያጣው ቤቴ ፣  
እንዳይውጠው ወና  
እግዜያብሄር ፊት ሄዳ ፣  
ታድረስልኝ ጸሎት  
ሌላ ሴት ለምጀ፣ እሷን እንድረሳት  
እሷን ለመፈለግ ፣  
ምን አንከራተተኝ ከመቃብር ጓሮ  
ፍቅር እስከ መቃብር፣ ት..ት..ት..ት  
እሱ ቀርቷል ድሮ፡፡

ጊዜው አማረ  
ባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ @2007

# በአድዋ ድል - ማንነት፣ አንድነት፣ ነጻነት...

ከገጽ 9 የዞረ

ጭስ ነጻነትን እያሸተቱ ወደፊት ገፉ፡፡ በርግጥ የጠላት ጦር የተጠናከረ ስለነበር የኢትዩጵያ ጦር መቀሌ ላይ እንደ አምባላጌ በቶሎ ድል ማድረግ አልተቻለውም ነበር፡፡ ኢትዮጵያውያን መቀሌ ላይ የመሸገው የጣልያን ጦር ጠንካራ እንደሆነ ስለተገነዘቡም ፊት ለፊት ከመጋፈጥ ከቦ መፈናፈኛ በማሳጣት አበሳውን ያስቀቶጥረው ጀመር፡፡ በተለይ በዚህ ወቅት በብልኂ እተጌ ጣይቱ የተነደፈው የውሃ ምንጭ መስመራቸውን የመዝጋት ስልት ከፍተኛ ሚና የነበረውና የሚደነቅ የውጊያ ስልት ነው፡፡ ከምንጩ መዘጋት በተጨማሪ በተደጋጋሚ የደረሰበትን ጥቃት መቋቋም ሲሳነው ቦታውን ለቆ ለመሄድም ድርድር ግድ አለው፤ “አስቀድሞ ቢለምኑት እምቢ ያለውን በኋላ ግን ሰው ስላለቀበትና ስለተቸገረ ምሽጉን ለመልቀቅ መፍቀዱን ላከ፡፡... በተከበበ በሁለት ወሩ የመቀሌን ምሽግ ለቆ መሳሪያውንና ስንቁን ቁስለኛውን ሰብስቦ ተነሳ..” (ተክለ ጻድቅ መኩሪያ 2000)፡፡ ጣልያውያን ከአለፈ ሽንፈት መማር እንኳን ተስኗቸው መቀሌ ላይም ለውርደት ተዳረጉ፡፡

ከመቀሌው ውጊያ ታሪክ ሌላው አስገራሚ ሁነት አፄ ምኒልክ ምርኮኞቹን ከነመሳሪያቸው መሸኘታቸው ነው፡፡ ይህንን ጉዳይ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ “አፄ ምኒልክም በግፍ አገራቸውን ለመውሰድ መጥቶ ጦርነት የገጠማቸውን ጠላታቸውን የያዘውን መድፍና ብዙ የጦር መሳሪያ ማርከው እሱንም ጦርነቱን እንደ ዝመረ ከነሰራዊቱ እዚያው እምሽጉ ውስጥ ለመፍጀት ሲቻላቸው ሳለ እንደገና ለጠላታቸው ስንቅና እቃውን የሚጭንበት አጋስስ ከሸኝ ጋር መላካቸው የአለም ህግ ጠባቂ መሆናቸውን ያስረዳል” ይላሉ፡፡ አፄ ምኒልክም ይህ ማድረጋቸው እንደ ፍርሃትና ቂልነት እንዳይቆጠርባቸው የላኩት መልዕክት አድናቆትንና አግራሞትን ይፈጥራል፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም “መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ” (2005) በሚል መጽሃፋቸው ፀሃፌ ትእዛዝ ገ/ስላሴን ጠቅሰው ካሰፈሩት ቀንጭቤ ላካፍላችሁ፤ “በእጀ ጨብጫቸው በእግሬ ረግጫቸው የነበሩትን እነዚህን አልነካቸውም፤ አንተው እንደተመኘሸው ሰጥቼ እሰድልሃለሁ፤ ነገር ግን...የሞኝነት እንዳይመስልህ ስለፍቅር ያደረግሁት ነው፤...አሁንም ብትታረቅም ድንቅ ጦርነትም ከከጀላችሁ እነዚህን ጨምራችሁ ጠቅላችሁ ኑ፡፡” እዚህ ላይ

“... ተማራኪው ባዙቅ ውሃ ውሃ ሲል

ዳኛው ስጠው አለ ሰላሳ በርሜል

እንደ በላኤ ሰብእ እንደመቤታችን

ሲቻለው ይምራል የኛማ ጌታችን” (ተ/ጻድቅ መኩሪያ 2000’110) የሚለውን ያስታውሷል፡፡

እናም የአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያዊያን የተዋጉት ጭቆናን ለመከላከል ነጻነትን ለማስከበር እንጂ ሊወጋ የዘመተን ሰባዊ ክብር ለማዋረድ ወይም ለማረድ እንዳልሆነ አፄ ምኒልክ ምርኮኞች ላይ ባሳዩት ርህራሄ አስረግጠን የመንፈስ ልዕልናችንን ለዓለም የገለጥንበት ልዩ ታሪካዊ ክስተት ነው፡፡ በተጨማሪ እምየ ምኒልክ ለሙሴ ሽፍኔ ከአድዋ ዘመቻ በኋላ የጻፉት ደብዳቤ ይህን ይደግፋል፤ “በጥጋባቸው አድዋ ላይ ተዋግተው ድል ሆኑ፡፡ እኔ ግን በድንቁርናቸው ብዛት የነዚያን ሁሉ የክርስቲያን ደም በከንቱ መፍሰሱን እያየሁ ድል አደረግኋቸው ብየ ደስ አይለኝም...” (ጳውሎስ ኞኞ 2006’ 159) ለነጻነት ትግል ጠሊቅ ትርጉም የሚኖረው ራስን መስዋት ለማቅረብ በማመን እንጂ ሌሎችን ለማረድ በማለም አይደልም ልበል እንዴ?!

እምየ ምኒልክ እንደገመቱትም የተለቀቁ ምርኮኞችን በመጨመር ከስምምነት ጦርነት መርጠው የካቲት 1896 አድዋ ላይ ተኩስ ከፈቱ፡፡ የእርቅና የሰላም አማራጭ እንዳከተመላቸው የተረዱት ምኒልክ “ግፋ በለው” አሉ፤ የምኒልክ ጦርም መዓቱን ሲያወርድ ጣልያን አረፋ ትደፍቅ ጀመር፡፡ አድዋ ላይ ጣልያን ማቃሰት ስታበዛ የተወሰኑ አውሮፓውያን ልባቸው ድው ደው አለባቸው፡፡ ሌሎች ቅኝ ገዥ መንግስታት ደግሞ የውርደት ወሬ ያዘለ ነፋስ በጆሮዋቸው ሲገባ “በአፍረካ ምድር ምኑን ሊያሰማን ነው”ይሉ ጀመር፡፡ ከቀን ወደ ቀን ‘ጣልያን በኢትዩጵያ ተሸነፈች’ የሚለው ወሬ በስፋት ተናፈሰ:: ጥቂቶች የጠላት ወሬ ነው ለማለት ዳዳቸው፡፡ የተቀሩት ህልም አድርገው የሚል ጸሎት በለሆሳስ ደገሙ፡፡ እውነትን የቀጣፊ ጸሎትም ሆነ የግብዝ ጆሮ ዳባ ልበስ ማለት ወደ ህልም ሊቀይር አይቻልምና ውሎ አድሮ ጣልያን አድዋ ላይ ግባተ መሬቷ መፈጸሙ ከሁነኛ ምንጭ ሰሙ፡፡ የኋላ ኋላም ጣልያን ሲሰርቅ እጅ ከፈንጅ እንደተያዘ ብላቴና አንገቷን ደፍታ በቀይ ባህር አካባቢ ስትቅለሰለስ ለመታዘብ በቁ፡፡ ቅኝ ገዥዎች በትምክህት ጥቁር ነጭን ሊያሸንፍ አይችል እንዳላሉ በዚህን ጊዜ የውርደት ምች አጠናገራቸው፤ አገረጣቸው፡፡ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ደግሞ የድሉን ውጤት እንዲህ ገልጸውታል፤ “በአድዋ ጦርነት የአውሮፓ መንግስታት ተረበሹ፡፡ ኢጣልያ በአድዋ ላይ የደረሰባት ውርድት የአውሮፓ ውርደት ሆነ፡፡ የኢትዩጵያም ድል የአፍሪካ የጥቁር ህዝብ ድል ሆነ”፡፡ በአጭሩ የአድዋ ድል ቅኝ ገዥዎችን ከል አልብሶ ጥቁሮች የነጻነት አክሊል ይደፉ ዘንድ የድፍረትን ምስጢር ቁልፍ አስጨበጣቸው፡፡

እዚህ ላይ የአድዋ ድል አውሮፓውያን ስለሌሎች ህዝቦች በተለይ ጥቁሮች የነበራቸውን ግንዛቤ ያረቀ እንደሆነ መገንዘብ አለብን፡፡ እንዲያውም በዚህ ጊዜ ድፍን አውሮፓ እንደነሱ ሰው መሆናችንን ከመመስከር አልፈው ‘ከእኛ በላይ ቢሆኑ ነው እንጂ’ ብለው በማሰብ የግሪካውያን ሆሜር ዝማሬ ያስተጋቡ ይመስለኛል:: የሆሜር መዝሙር እነሆ

“እናንተ ኢትዮጵያዊያን ከሰው ዘሮች ሁሉ እንከን የሌላችሁ

ከተንኮል ከክፋት ከሰው ድክመት ሁሉ ነጻ የሆናችሁ

ከቶ ከምን ይሆን የተፈጠራችሁ ምንድን ነው ባህሪያችሁ?

እግዜሮች ትሆኑ ወይስ ሰዎች ናችሁ?”

(ሀዲስ አለማየሁን ጠቅሶ በወቅቱ ስዩም ካሰፈረው የተቀዳ)

አዎ! የአድዋ ዘመቻ ጥቁር ህዝቦች የነጻነትን ጣዕም የሚያውቁና ለዚህም ህይወት እስከመክፈል ቆራጦች እንደሆኑ በሚገባቸው መንገድ ያስተማርንበት “ጉባኤ” ነበር፡፡ የነጻነት መሰረቷ ዘር አለመሆኑን ለማይረዳ ግብዝ እንዲህ የሰብአዊነት ወዝ በጠገበ አለንጋ እየሸነቆጡ ከማስረዳት ውጭ በዚያን ጊዜ ምን አማራጭ ነበር!

የአድዋ ድል አውሮፓውያን ሲኩራሩበት የነበረን ስልጣኔ እንዲመረምሩ ከማድረጉ በተጨማሪ ጥቁር ጀግናን በማድነቅ እና በመደገፍ ሰብአዊነት የተላበሰ ታሪክ እንዲሰሩም እድሉን የፈጠረ ይመስለኛል፡፡ ለምሳሌ “የሮም ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በመንግስታቸው ላይ ተቃውሞ በመውጣት “ቪቫ ምኒልክ! ...ምኒልክ ህያው ይሁን!” በማለት የኢትዮጵያን ንጉስ ሲያወድሱ ተደምጠዋል፡፡ የተማሪዎች ተቃውሞ ምናልባትም በአውሮፓ ታሪክ በዓይነቱ የመጀመሪው ሳይሆን አይቀርም” (ሙሉቀን 2006)፡፡

የአድዋ ጦርነት/ድል ለእኔ ኢትዮጵያዊያን የተዋጉት ጭቆናን ለመከላከል ነጻነትን ለማስከበር እንጂ ሊወጋ የዘመተን ሰብአዊ ክብር ለማዋረድ ወይም ለማረድ እንዳልሆነ አፄ ምኒልክ ምርኮኞች ላይ ባሳዩት ርህራሄ አስረግጠን የመንፈስ ልዕልናችንን የገለጥንበት፤ የሰው ህይወትን በመክፈል የነጻነትን ዋጋ ለአለም ያስተማርንበት (ለነጻነት ከሰው በላይ የሚመጠን ክፍያ ባለመኖሩ!) እንዴት ሰባዊነትን ከጦርነት አቀዳጅቶ ነጻነትን ማስከበር እንደሚቻል ያሳየንበት ሰባዊ ድል ነው፡፡

ለማጠቃለል ጅጂን (የሙዚቃው እተጌ ጣይቱ) እናስገባት

“የተሰጠኝ ህይወት ዛሬ በነጻነት

ሰው ተከፍሎበታል ከደምና ከአጥንት”

ማሳሰቢያ- ይህ ጽሁፍ “አድዋ” በሚል ርዕስ በናይል ጋዜጣ (2006 ዓ.ም) ካቀረብኩት ጋር ከአቀራረብና ይዘት አንጻር ተመሳሳይ ቢሆንም ብዙ ማሻሻያዎች ተደርጓል፡፡

ፍቅር ምክሩን ይስጠን

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን ይሰራል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ ናቸው የሚሏቸውን

- የተለያዩ ጹህፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በአድራሻችንና በኢሜል መላክ ወይም በአካል በመምጣት መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት ከጥር 23 እስከ የካቲት 8 /2007 ዓ.ም ድረስ በተካሄደው 8ኛው የኢትዮጵያ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች የስፖርት ፌስቲቫል ላይ የተሳተፈው የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ልዑካን በከፊል














ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ